# *የግንቦት 97 ምርጫ፣ ቅንጅትና የወደፊቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ የትግል አቅጣጫዎች*

**ማስታወሻ፤**

*በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ይህንን ጽሁፍ የማቀርበው በግሌ እንጂ ቅንጅትን በመወከል አይደለም። ይህ ጽሁፍ የተጻፈው* December 2005 *ነው። የጽሁፉ አላማ በወቅቱ ወያኔ በቅንጅት ላይ በወሰደው እመቃ የተነሳ ተፈጥሮ የነበረውን የፖለቲካ አመራር ችግር በመገንዘብ በሃገር ውስጥ ከእስር የተረፉትና ከከሃገር ውጭ ደግሞ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች የሆኑት የሚወያዩበትን ሰነድ ለማቅረብ ነበር። ወቅቱ አስቸጋሪ በመሆኑና በተለይ ከጥቂት ግለሰቦች በስተቀር ማን የቅንጅት አባልና ደጋፊ እንደሆነ በሚገባ የማውቅበት ሁኔታ ባለመኖሩ የተነሳ ጽሁፉን በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ያዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከእዚህ በተረፈ በሃገር ውስጥም ጥቂቶች እንዲያዩት ሆኗል። ባሁኑ ወቅትም ብዛት ያላቸው የቅንጅትና የሌሎች ድርጅቶች ደጋፊዎች እንዲህ አይነቱን ጽሁፍ በማንበብ የሚጠቀሙ ስለመሰለኝ እንኝህን አንባቢዎች መድረስ በሚቻልበት ብቸኛው መንገድ በድረ-ገጽ እንዲወጣ አድርገያለሁ።*

*ከእዚህ በተጨማሪ በሃገር ቤት ወያኔ የወሰደው እመቃ አስከፊነት የውጭውን ትግል አስፈላጊነት ያጎላውና ሁላችንም በውጭ የምንገኘውን ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጠንካራ ህብረት የሚጠይቅ ይሆናል ብዬ በማማኔ ይህን ጽሁፍ ከቅንጅት ጋር ተባብሮ ለመስራት በወቅቱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለነበሩት የህብረቱ የአመራር አባላት መሃል ለጥቂቱ እንዲደርሳቸው አድርጊያለሁ። ሌላው ቢቀር በቅንጅት ውስጥ ከምንገኝ ግለሰቦች መሃል የመተባበርን አስፈላጊነት የምንረዳ መኖራችንን በማሳየት እንዴት መተባበር ይቻላል በሚለው ጥያቄ ላይ ግልጽ ወይይት ማድረግ እንዲቻል በማሰብ ነበር።*

*ይህ ጽሁፍ በተጻፈበት ወቅት የአለም አቀፍ አመራር የሚባል ነገር አልነበረም። ትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ ሊፈጠር መታሰቡን አላውቅም ነበር። ይሁንና አንድ አይነት አመራር በውጭና አንድ አይነት ትብብር አስፈላጊ እንደሆነ በጥቅሉ አስቀምጬ ለማለፍ ሞክሪያለሁ። የትብብሩ መፈጠር እና አንደ አላማው ያስቀመጠው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ያቀፈ ጉባኤ፣ ቅንጅት ፓርላማ ለመግባት ያስቀመጣቸውን 8 ነጥቦች ያካተተ እና የተሻገረ ሆኗል የሚል እምነት አለኝ። ይህንን ጽሁፍ ስናነብ ወያኔ እንደ መንግስት በመቀጠል ቀድሞ ቅንጅት ያቀረባቸውን 8 የመደራደሪያ ነጥቦች ምላሽ ሰጪ የሚሆንበት ሁኔታ እራሱ በወያኔ እርምጃዎች ያበቃለት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። በትብብሩ ሰነድ ላይ እንደሰፈረው ከአሁን በኋላ የነጻ ተቋማት ምስረታ ወያኔ እንደ አንድ ፓርቲ የሚሳተፍበት የሃገር አቀፉ ጉባኤው የውይይት ሂደት ውጤት ብቻ ነው። ይህ ካልሆነም የሃገሪቱ የፖለቲካ ሂደት በሌላ መንገድ የሚወስነው ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ወያኔ ስልጣን ላይ እንደ መንግስት ተቀመጦ በእዚህ መንግስት ስር ከተቃዋሚዎች ጋር በመደራደር በሚፈጠር ነጻ ኮሚሽን አማካይነት እንዲፈጸም ታስቦ በቅንጅት ለድርድር የቀረበው የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ወያኔ በወሰደው ግፈኛ እርምጃው ከቀየረው ሁኔታ ጋር ተቀይሯል። በቅንጀት በኩል የመታገያችን ነጥብ መሪዎቻችንና ሌሎቹም የህሊና እስረኞች ይፈቱ፣ በሃገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ የሚያገባቸው ሃይሎች በሙሉ የተሰባሰቡበት የሰላማዊ ሽግግር ተላሚ ገባኤ ይጠራ ከማለት ውጭ መሄድ የሚችል አይሆንም።*

ሌላው ማስታወሻዬ ሁሌም እድል ባገኘሁ ቁጥር ለመግለጽ የምሞክረው ነው፡፡ በሃገር እና በወገን ጉዳይ ላይ የምንጽፈውን ጽሀፍ በተቻለ መጠን ብንጨነቅበት፣ እኔም አለሁ ለማለት ብቻ በሚገባ ያለተፈጨ ሃሳብን በሁለት በሶስት ገጽ ቋጥረን በየግዜው በሚመጣው መሄጃውን እና መድረሻው በውል በማይታወቀው ሰረገላ ላይ መፈናጠጡን እንተወው የሚለው ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በሀገር እና በወገን ጉዳይ ላይ የምንጽፈውን ሁሉ አብዛኛው የሃገራችን ሕዝብ ሌላው ቢቀር ማንበብ የሚችለው ህዝብ በሚገባው ቋንቋ ብንጽፈው፣ በተለያዩ ምክንያቶች የማንችልም ከሆነ በሰው ብናስተረጉመው ጥሩ ነው፡፡ ከውጭ በሚሰራጩ ሬድዮኖች ሊነበብ ይችላል፡፡ በሀገር ቤትም ከኢንተርኔት አውርዶ አባዝቶ ማሰራጨት የተለመደ ሆኗል፡፡ የሃገሬውን ሕዝብ በአንባቢነት ማሳተፍ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ እወቀትና መረጃ ጉበልት ነው፡፡ የሕዝብን ብቃትና ብስለት ማጠናከሪያ መሳሪያ ይሆናል፡፡ የማወራው ጽሁፍ ለፈረንረጆቹ የምናቀርበውን የአማልዱን ደብዳቤ ወይም በራሳችን መሃከል ለእንካ ሰላንተያ የሚጻፈውን ማለቴ አይደለም፡፡ በመጨረሻም እባካችሁ ሳናዳምጥ ለመናገር እንደሚቀናን ሁሉ፣ ሳናነብ ለምላሹ ብእር ማንሳት፣ ትልቅ የባህላችን በሽታ መሆኑን አውቀን መድሃኒቱን እንፈልግለት፡፡ አንዱም ለመቀራረብና አብሮ ለመስራት እንቅፋት የሆነው በተለይ በአሁኑ ግዜ መሰረታዊ ልዩነቶች ሰላሉን አይደለም፡፡ የምንቃወመውን ብቻ በማሰላሰል ስለምንሰማና ሰለምናነብ ነው፡፡ ቅድሚያ ለመቀራረብ በሚሰጥ መንፈስ ሁሉን እንፈትሸው፡፡

በመጨረሻ ቀደም ብዬ በword የጻፍኩትን የእዚህን ጽሁፍ ቅጂ ማግኘት ስላለቻልኩ ይህንን ማስታወሻ ለመጻፍ ስል በPDF ታስሮ የነበረውን ለመፍታት ተገድጃለሁ፡፡ በእዚህም የተነሳ በየገጾቹ ሊታይ ሰለሚችለው የአርትኦት ችግር አንባቢን በቅድሚያ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ በአሁኑ ወቅት ይህንን ጽሁፍ ለማቅረብ የተገደድኩት ወደፊት መጻፍ አለባቸው ብዬ ባሰብኳቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ የሚቀርበውን፣ አንባቢ እንዲረዳ ያስችላል ከሚል እምነት ነው፡፡ በወቅቱ በየድረገጹ የምናየው ወደ ጋጠ-ወጥነት የሚጠጋ የተዋስኦ (discourse) ባህል እያስበረገጋቸው ለስማቸው እና ለግል ክብራቸው ሲሉ አንገታቸውን መድፋት የመረጡት በርካታ ሃገር ወዳድ ምሁራን ብዙ ትንተና በሚያስፈልገው የሃራችን ጉዳይ ላይ በድፍረት እንዲጽፉ ለማበረታት ነው፡፡ ተራ ስምና ክብር ከሃገር እና ከወገን በላይ ትርጉም የላቸውምና የሚጻፈውን እያነበቡ ወይ ጉድ ከማለት አልፎ ገንቢ አስተያዬት መለገስ የዜግነት ግዴታችን ነው፡

## ***መንደርደሪያ***

## ***ወደፊት ለመጓዝ ወደኋላ የመመልከት አስፈለጊነት፣***

ወገኖቻችን በሽዎች እየሞቱ፣ እየታሰሩ እና እየተሰቃዩ ነው፡፡ ይህ በወገን ላይ የሚደርስ በደል እርጋታ እንዳናገኝ አድርጎናል፡፡ ህሊናችን እና አንጀታችን ሲቃጠል፣ እንቅልፍ አጥተን የምናድረው ብዙ ነን፡፡ ቢጠቅም ባይጠቅምም ህሊናችን አንድ ነገር እንድናደርግ ይጎተጉተናል፡፡ በሃገር እና በሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው በደል በጣም የሚሰቀጥጥ በመሆኑ፣ የወያኔን ዘረኛ እና ግፈኛ አገዛዝ ጠራርጎ ለመጣል አንድ ተአምራዊ ሃይል በእጁ እንዲገባ ሲመኝ የሚውለው ብዙ ነው፡፡ በየከተማው እና በየገጠሩ ባልተደራጀ እና ግብታዊ በሆነ መንገድ እያመጸ ከወያኔ የአፈና መዋቅር ጋር የሚላተመው ተበራክቷል፡፡ አርሶ አደሩ በገጠር በራሱ መንገድ የተጫነበት ዘረኛ እና አምባገነናዊ መርገም ከአናቱ ላይ ለማራገፍ እርምጃ እየወሰደ ነው፡፡ በከተማም የአንዱ የህብረተሰብ ክፍል ተቃውሞ በወያኔ ሲመታ፣ ሌላው የህብረተሰብ ክፍል እየተነሳ ከወያኔ የአፈና መዋቅር ጋር በድፍረት እየተጋፈጠ ነው፡፡ እድሜያቸው ከአስር አመት ብዙም የማይበልጡ

ህጻናት ተማሪዎች ሳይቀሩ «እምቢ ለዘረኛው አሸባሪ የወያኔ አምባገነናዊ መንግስት» በማለታቸው በዱላ እንደእባብ እየተቀጠቀጡ ነው። ከወላጆቻቸው ጉያ ተገንጥለው በየገጠሩ በሚገኙ የማጎሪያ ጣቢያዎች ተወስደዋል። በውጭ ሃገር የሚገኘውም ኢትዮጵያዊ፣ የተቃውሞ ሰልፍ፣ የሻማ ማብራት፣ የረሃብ አድማ እና የእርዳታ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ያደርጋል። የመለስ ዜናዊን እጅ መጠምዘዝ ለሚችሉት የውጭ መንግስታት የተማጽእኖ ደብዳቤ ይጽፋል። በአካልም በየመንግስታቱ ቢሮ በመገኘት ደጅ ይጠናል። በሃገራችን ውስጥ ዘረኛው የወያኔ መንግስት በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው ተሰፍሮ የማያልቅ ግፍ እየባሰበት በሄደ ቁጥር የሁሉም መዋከብ እየጨመረ ሄዷል።

በውጭ ሃገሮች የሚገኘው ኢትዮጵያዊ እንዲህ እንደዛሬ በአንድነት በአደባበባይ በወገኖቹ እና በሃገሩ በደል ዙሪያ ተንቀሳቅሰ አያውቅም። ከግለሰብ ደረጃ አንስቶ በትንንሽ እና በትልልቅ ቡድኖች በመሰባሰብ ለተጎዱ ወገኖች እርዳታ ለማድረስ፣ እንባቸውን ለማበስ የሚያደረገው ጥረት የሚያስደንቅ ነው።ይህም ሆኖ አሁን ካለንበት በወከባ ከተሞላ ሁኔታ ለደቂቃ ወጣ ብለን በመቆም ከላይ ከጠቀስናቸው በጎ ድርጊቶች ባሻገር የሀገራችንን ሕዝብ መከራ እና ስቃይ ለዘለቄታው ለማስቆም ምን መደረግ እንዳለበት እያሰብን አይደለም።

በሃገር ቤት እንዲህ አይነቱን የማሰብ ስራ መስራት የሚችሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች በማፍረስ፣ መሪዎችን በማሰር እና በመግደል አርቀን እንዳናይ ወያኔ እያዳከመን ነው። የቀሩትንም ተገናኝተው መምከር በማይቸሉበት ሁኔታ በሰላዮች እና በጸጥታ ሃይሎች ገድቧቸዋል።

የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ ነጻነት ሕዝብ ተገፎ፣ መሰብሰብ እና መናገር የሚችሉት በጋዜጣ፣ በየሬድዮ እና በቴሌቪዥን እድል የሚያገኙት የወያኔ ባለስልጣናት እና ወያኔ ለራሱ አምባገነናዊ ስርአት መጠናከር ይጠቅሙኛል፣ የሕዘቡን የትግል አንድነት ያፈርሱልኛል ብሎ ያመነባቸው ግለሰቦች እና ቡድኖች ሆነዋል። ሰላዮቹ እና ቅጥረኞቹ እንደልባቸው ጋዜጣ ማሳተም ሳያንሳቸው ዛሬ ደግሞ በወያኔ መሪ በመለስ ዜናዊ እና በባለቤቱ በወይዘሮ አዜብ ካፒታል የተቋቋሙ፣ እንደ  ኢፍቲንእና እንደ ሪፖርተር ጋዜጠች ከስላለ እና ከደህንነት መዋቅሩ ጋር የሚሰሩ የሬድዮ ጣቢያዎች በነጻ እና የግል ሬድዮ ጣቢያ ስም በሕዝብ ላይ የሚያናፉበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ማለቂያ በሌለው የወያኔ የሃሰት ክስ እና የፕሮፓንዳ ጥቃት መከላከል ተጠምደን፣ የታሰሩት መረዎቻችን፣ ይፈቱ! ግድያና እስራቱ ይቁም የሚሉ ጥያቄዎችን በተበታተነ መልኩ ከማንሳት የሚያልፍ ተግባር እንዳንፈጽም ተድርገናል። እነዚህን እና ሌሎችንም መሰረታዊ የመብት እና የነጻነት ጥያቄዎች በተቀናጀ እና በተደራጀ መልኩ ማንሳት በሃገራችን አይታይም። እውነታው ይህ ነው።

በአርስቱ እንደተጠቆመው፣ ወደ ኋላ መመልከቱ ከዛሬ ሰላሳ አመት በፊት በሃገራችን የፖለቲካ ስርአት ለውጥ ለማምጣት ሙከራ ከተጀመረበት ወቅት ቢጀምር ጥሩ ነበር። ሃገራችን አሁን ካለንበት ወቅት ጋር ተመሳሳይነት በነበራቸው የታሪክ ወቅቶች አልፋለች። በእነዚህ ወቅቶች የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና አጠቃላዩ የፖለቲካ ልሂቅ ከአካበታቸው ልምዶች የዘመናችን ሰው ብዙ መማር ይችል ነበር። የፖለቲካ ልሂቁ፣ ሕዝብን እና ራሱን በተከታታይ ለመጡ አምባገነን ገዥዎች እንዴት እንዳጋለጠ፣ እንዴትስ የአምባገነኖችን እድሜ ለማራዘም እንደቻለ ማጤኑ ጠቀሜታ ይኖረው ነበር። ባለፈው የተሰሩት ስህተቶች ምን እንደነበሩ በማጤን፣ አሁን ላለንበት ወቅት ጠቃሚ ትምህርት መቅሰም ይቻል ነበር።

እንዲያው ባጭሩ ግን ብዙዎቻችን እንደምናስታውሰው የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የፖለቲካ ልሂቃኑ በአንድነት መስራት አልቻሉም ነበር:: ሁሉም ጠባብ የድርጅት ጥቅም በማስቀደም፣ ከሃገር እና ከወገን ጥቅም በፊት ለስልጣን መጠላለፉ ቅድሚያ ሰጡ:: የፖለቲካ ልሂቃኑ በገጠሟቸው ሰው በላ ስርአቶች ፊት በህብረት አለመታገላቸው፣ ሊያስከትል ስለሚችለው ችግር አላሰብ አሉ:: ሕዝብ በቀላሉ ሊገባው እና ሊዋደቅለት የሚችል የጋራ የትግል ጥሪ በማድረግ፣ በእዚህ የትግል ጥሪ ዙሪያ በጋራ ለመቆም አልሞከሩም:: ወቅቱ አጣዳፊ እና አዋካቢ በነበረበት ጊዜም ቢሆን ትንሽ ቆም ብሎ፣ ትንፋሽን ያዝ አድርጎ፣ ሁኔታዎችን ለመመርመር ያለውን ጠቀሜታ አልተረዱም:: አምባገነኖች በየግዜው የሚጭሩትን እሳት ከኋላ ኋላ እየተከተሉ ለማጥፋት ከመሯሯጥ ይልቅ፣ ከፊት ቀድሞ ሕዝብን መምራት የሚችሉበትን ሁኔታ ማደራጀት አልቻሉም:: ያለፈው ታሪካችን እነዚህ እና ሌሎችንም ጠቃሚ ትምህርቶች ሊቀሰምበት የሚችል እንደ ነበር አድርጎ መውሰድ ያቻላል::

የግንቦት 1997ቱ ምርጫ ሲመጣ ወይም ከእዛ ቀደም ብሎ በነበሩት 14 የወያኔ ዘረኛ የግዛት ዘመናት በሃገራችን እና ከሃገራችን ውጭ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከላይ ከጠቀኩት የፖለቲካ ታሪካችን እና ተመክሮአችን በቂ ትምህርት ለመቅሰም ሞክረው የነበሩ ስንቶቹ ናቸው? የእዚህ አይነቱን ካለፈ የፖለቲካ ታሪካችን መቀሰም ስለሚገባው ትምህርት ትኩረት ሰጥተው ጥናት በማድረግ፣ የፖለቲካ ድርጅቶቻቸው እና የአባላቶቻቸው መመሪያ እንዲሆን በማድረግ የተንቀሳቀሱ ስንቶቹ ናቸው? የፖለቲካ ልሂቁ በመከፋፈሉ ለደርግ መጠናከር እድል እንደሰጠ ሁሉ፣ ይህንን መከፋፈል በጊዜ አስወግዶ ዝግጅት ባለማድረጉ በ1983 ለወያኔ የስልጣን መያዝ አመቺ ሁኔታ እንዳዘገጀ ሁሉ፣ አሁንም መከፋፈሉ የወያኔን ዘረኛ ስርአት በማጠናከር ሊጫወት የሚችለውን አደገኛ ሚና በውል የተረዱ ስንቶቹ ናቸው? ምንድ ነው በፖለቲካ መስኩ ሀሌም ከሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ የወከባ አዙሪት እንዳንወጣ እያደረገን ያለው?

የግንቦት 1997 የምርጫ ውድድር ከመጀመሩ በፊት አና በኋላ የሃገሪቱ ሁኔታ በፍጥነት ይቀያየር እንደነበር ይታወቃል:: በሕዝብ ቁጣና መነሳሳት በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ ለከፋ እና ሴራ እየተቀደሙ ትግሉን ከፊት ለፊት መምራት ሳይሆን ከኋላው በተጎታችነት የመሄድ አደጋ እንደሚከሰት ካለፈ ልምዳችን በመነሳት አስቀድመው ያዩ ነበሩ ወይ? የነበረውን ጠባብ እድል በመጠቀምም ቢሆን ይህንን አደገኛ እና አስቸጋሪ ሁኔታ በፍጥነት የመቀየር አስፈላጊነት ተረድተው የተንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች የትኞቹ ናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች የተነሱት እያንዳንዱን ድርጅት በሚመለከት የተጠያቂነት ድርሻ ለማከፋፈል አይደለም:: ያለንበትን ሁኔታ ለማመላከት ብቻ ነው::

በጥቅሉ ግን በህብረት ለመመስራት የተደረገው ሙከራ በቂ አልነበረም:: ካለፈው ታሪካችንን በመማር በህብረት ባለመስራት ሊመጣ ስለሚችለው አደጋ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም:: ሁሉንም የሃገሪቱን የፖለቲካ ልሂቃን እና ሕዝብ በጋራ ሊያሳትፍ የሚችል የፖለቲካ ጥያቄ በማንሳት፣ በእዚህ ጥያቄ ዙሪያ ተሰባስቦ የጋራ ጥሪት ለማድረግ አልተቻለም:: ወያኔ በየግዜው የሚጭረውን እሳት ለማጥፋት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን ስለትግሉ የአጭር እና የረጅም ግዜ ስልቶች እና ግቦች የማሰብ አስፈላጊነት በመረዳት አርቆ እያሰቡ ለመንቀሳቀስ አልተሞከረም:: ሀገራዊ እና ወገናዊ ጥቅሞች ሳይሆኑ የግለሰቦች እና የቡድኖች ጠባብ ስሜት እና ፍላጎት በድርጅቶች ግንኙነቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ ተደርገዋል:: እነዚህ

እና ሌሎችም ችግሮች ከግንቦቱ 1997 ምርጫ ጋር አልተሳሰሩም ነበር ብሎ መካድ አይቻልም። አሁንም በቀጣይነት የምናያቸው ችግሮች ናቸው።

አሁን ባለንበት ወቅት፣ ሕዝብ በወያኔ ላይ ያለው ምሬት ከመቼውም በላይ ገዝፏል። የወያኔም የዘረኛ አምባገነናዊ መንግስት በሕዝብ ላይ የሚፈጽመው ግፍ ገደብ አጥቷል። በፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል መኖር የሚገባው ህብረት እየጨመረ ነውን? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ መልሱ አይደለም እንደሆነ እናውቃለን። እንኳን በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ቀርቶ በአንድ ድርጅትም ውስጥ ያለው አንድነት አስተማማኝ ያልሆነበት ደረጃ ላይ እየደረሰ እንደሆነ ግልጽ ነው። የፖለቲካ አመራር መስጠት የሚገባቸው ሃይሎች የአጭር እና የረጅም ግዜ እቅዶች ይዘው እየተንቀሳቀሱ ነውን? ወይም ወያኔ በየግዜው የሚጭረውን እሳት በማጥፋት ስራ ላይ ብቻ ተጠምደዋል? የተፈጠረውን የሕዝብ መነሳሳት በተናጠል ለመምራት የሚያስችል አቅም እንዳለቸው በደንብ ሳይገመግሙ በየግላቸው ለመራወጥ የሚንቀሳቀሱት ሃይሎች እየበረከቱ ነው? ወይም እያነሱ ነው? ድርጅታዊ መጠላለፉ ነው ቅድሚያ የተሰጠው? ወይስ ከግለሰቦች ከደርጅቶች ህልውና እና ጥቅም በላይ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ የሕዝብ፣ የሃገር ህልውናና ጥቅም፣ የትኛው ነው? ለእዚህም ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው።

ዛሬ ወያኔ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና በአጠቃላዩ የሃገራችን ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል ከማጋለጥና እንዲቆም ለማድረግ ስልጣን አላቸው ብለን ከምናስባቸውን የውጭ መንግስታት እርዳታ ከመጠየቅ ውጭ ብዙ እየሰራን አይደለም። ይህንንም ቢሆን ብቃት እና ችሎታ ያለውን ግለሰብ ቡድን እና ድርጅት ባቀፈ መልኩ ሳይሆን፣ በተበጣጠሰ የሰው ሃይል የእውቀት እና የገንዘብ ብክነት በሚያስከትል እርስ በእርሳችን እየተጠላለፍን የምንሰራው ነው። የሕዘቡን ቁጣ መሰረት ያደረጉ የፖለቲካ ጥያቄዎች በማንሳት በሃገር ውስጥ እና በሃገር ውጭ ያለው ሃገር ወዳድ ዜጋ እና የፖለቲካ ድርጅቶች በማስተባበር እንዴት ይህንን ትግል ወደላቀ ደረጃ ማሸጋገር ይቻላል? የሚል ጥያቄ አናነሳም።

ከግንቦቱ ምርጫ ጋር በመያያዝ በተፈጠሩ ሁኔታዎች ስለ ሃገራችን የፖለቲካ እውነታ ምን አዲስ ነገሮች መገንዘብ ችለናልን? የሚለውንም ጥያቄ አንጠይቅም። የሚገርመው፣ ከግንቦቱ ምርጫ እና ከዛም በኋላ በመጡት ጥቂት ወራት ውስጥ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ስፍራ ሊሰጣቸው የሚገቡ፣ ወደፊት መደረግ የሚገባውን ትግል እና አቅጣጫውን የወሰኑ፣ በአስተማሪነታቸው ታላቅ የሆኑ ተመክሮዎች ተመዝግበዋል። እነዚህ ተመክሮዎች በደንብ ላሰበባቸወ፣ እስከ ዛሬ ድረስ ውስብስብነት የነበረውን የሃገሪቱ የፖለቲካ ጥያቄ ሁሉም ሕዝብ፣ የተማረውም፣ ትምህርት ያልቀሰመውም፣ ደሃውም፣ ሃብታሙም፣ ስልጣን ላይ ካለው ዘረኛ የወያኔ ቡድን በስተቀር ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል እውነታዎችን እንድንገነዘብ አስችለውታል። በፖለቲካ ድርጅቶች መሃል መቀራረብን፣ በአንድነት መስራትን እንዲሁም በሃገር ውስጥ እና ከሃገራችን ውጭ ባላው ሕዝብ መሃል በግልጽ የፖለቲካ አጀንዳ ዙሪያ ህብረት ሊፈጠር የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት የቻለ ነው።

የእዚህ ጽሁፍ አላማም እነዚህን የግንቦቱ ምርጫ ግልጽ ያደረጋቸውን እውነታዎች በማቅረብ የሚቀጥለውን የትግል አቅጣጫ መጠቆም ነው። የግንቦቱ ምርጫ በአጠቃላይ ግልጽ ያደረጋቸው ጭብጦች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መሃል በበኩሌ ትልቅ ትርጉም ያላቸውን የሚቀጥሉትን ነጥቦች አነሳለሁ።

- *የህሕዝብን የመነሳሳት ስሜት ትልቅነት በሚጋባ ያልተመዘነበት ሁኔታ፣*
- *የሕዝብ የፖለቲካ ብስለት የፖለቲካ ልሂቃኑን ሞግዚታዊ አመለካከት እንዳወላለቀው፣*
- *ፖለቲካ ከሰማይ ወርዶ በእውንም ምድራዊ እና ሕዝባዊ የሆነበት ሁኔታ መፈጠሩ፣*
- *ግንቦት 97 እና የሕዝብ ድምጽ መጭበርበር ያስከተለው ታላቅ የፖለቲካ ግንዛቤ፣*
- *የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሌሎችም የሲቪክ ማህበራት የጋራ አመለካከት እንዲኖራቸው በማድረግ ለጋራ የትግል አንድነት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠሩ፣*
- *ከተለወጠው ሁኔ.ታ አንጻር ቅንጅት ወዴት፣*
- *ቅንጅት እና ከማናቸውም የፖለቲካ እና ፖለቲካዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ የመስራትን አስፈላጊነት በሚመለከት፣*
- *ቅንጅት እና የአመጽ ትግል የሚያኪያሂዱ እንቅስቃሴዎች፣ እነዚህን ነጥቦች ዘርዝር አድርገን እንመልከት፣*

## *1- የሕዝብን የመነሳሳት ስሜት ትልቅነት በሚገባ አለመገንዘብ፣*

በእዚህ ነጥብ ላይ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች የተለያየ አቋም እንደነበራቸው እና አቋማቸውም በየግዜው እየተቀየረ እንደሄደ እናውቃለን። የትኛው ድርጅት ትክክለኛ ግምገማ ነበረው፣ የትኛውስ አልነበረውም የሚለው ጥያቄ ላለንበት ሁኔታ የሚያመጣው ፋይዳ የለም። በአጠቃላይ ግን የተቃዋሚው ወገን የሕዝብን ቁጣ፣ ለለውጥ ያለውን ፍላጎት፣ በወያኔ ላይ የነበረውን ምሬት ግምት ውስጥ በማስገባት በምርጫው ወቅት «ወያኔን ወግድልኝ» በማለት ሕዝብ ያሳየውን ቁርጠኝ እርመጃ ይገልጻል ብለው ያሰቡ በጣም ጥቂቶች ብቻ እንደነበሩ እናውቃለን። ይህ ሕዝብ፣ «በርካት ተጨማሪ ወንበሮች እንድንይዝ ከማድረግ አልፎ ወያኔን ከስልጣን ሊያባርር የሚችል የወንበር ብዘት አንድንይዝ ሊያደርግ ይችላል» ብለው ከልባቸው ያሰቡ ከነበሩም እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ለሚያስከትለው መዘዝ መዘጋጀት ነበረባቸው። የዝግጅቱ ጉድለት የሚያሳየው ነገር ቢኖር በ97ቱ ምርጫ ወያኔን የማሸነፍ ጉዳይ ከልብ የታመነበት ለመሆኑ እንድንጠራጠር የሚያደርግ ነው። «ወያኔ ሊሸነፍ ይችላል» ብሎ አስቀድሞ ያሰበ ፖለቲከኛ፣ «ወያኔ ቢሸነፍ ሊፈጽመው ስለሚችለው ወንጀል አላሰብኩም» ካለን ድርጊቱ እጅግ የሚገርም የፖለቲካ ልቅነትን የሚያሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። እንዲያው በድፍኑ የተቃዋሚው ወገን ከፍተኛው ክፍል የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫው ወቅት የፈጸመውን፣ ወያኔን በምርጫ የማስወገድ ተአምር ይሰራል ብሎ አልጠበቀም ነበር ማለቱ ይሻላል። ለምን ይህ ሆነ የሚለው ጥያቄ በርካታ ቁም ነገሮችን የያዙ መልሶችን ሊያስጨብጠን የሚችል ቢሆንም ያንኑ ያህል መውጫ ወደ ሌለው የክርክር ማጥ ውስጥ የሚዶለን ይሆናል። ይህ ደግሞ ካለነበት ሁኔታ አንጻር ለማንኛችንም አይጠቅምም።

በገዥው ፓርቲ በኩል በሁኔታው ላይ የነበረው ግምገማ ደግሞ ከተቃዋሚው ጎራ እጅግ የባሰ እና ከእውነታው የራቀ ነበር። ለወያኔ መንግስት ባለስልጣናት የሕዝብ ምሬት እና መንገፍገፍ ግልጽ ያልሆነበት ምክንያት ግን ለሁላችንም ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ፣ በመጠኑም ቢሆን መዳሰሱ ተገቢ ይሆናል። መንግስት እና ባለስልጣናቱ የሕዝብ ስሜት ምን እንደሚመስል ፍንጭ ማየት ያልቻሉባቸው

በስልጣናቸው ላይ እያሰገመገመ የነበረውን ሕዝባዊ ማእበል ማድመጥ እንዳይችሉ ያደረጓቸው ምክንያቶች ከብዙ ሁኔታዎች ጋር ይያዛሉ።

- የመንግስት አስተዳደር ህገ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል የሌለው በመሆኑ፣ የመንግስት ባለስልጣናት፣ በተለያየ ግዜ፣ ገና ከጅምሩ ከሀገር ጥቅምና ደህንነት አኳያ የፈጸሟቸውን በስልጣን መባለግ እና በሙስና መለወስ ያሳዩባቸውን ሁኔታዎች በህግ ለመጠየቅ የሚያስችል መንግስታዊ የሆነ ነጻ የፍትህ አካል አለመኖሩ፣
- መንግስታት እና ባስልጣናቱ ጉድፋቸውን ሳይወዱ በግድ ማየት እንዲችሉ ማድረግ የሚችለው ትልቁ እና የመንግስትን የስልጣን ብልግና ለመቆጣጠር ታላቅ ጉልበት እንዳለው የሚነገርለት ነጻ ፕሬስ ወይም ነጻ ሀገራዊ መገናኛ-ብዙሃን በሃገራችን አለመኖሩ፣
- ሃገር አቀፍ አቅምና ጉልበት ያላቸው የሙያ እና የሲቪክ ማህበራት የሌሉበት፣ ለመኖርም የሞከሩትን እንዲጠፉ በማድረግ፣ በእነዚህ ድርጅቶች መኖር መንግሰትና ባለስልጣናቱ ከሚያሳዩት ጋጠ-ወጥ የመብት መጋፋት እና ንቅዘት እንዲታቀቡ ለማድረግ አለመቻሉ፣
- የወያኔ ፓርቲ ስታሊናዊ አደረጃጀት እና አመለካከት፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲዊ መሪያቸውን መለስ ዜናዊን እና የሚመራውን ድርጅት በባእድ አምልኮት ደረጃ እንዲመለኩ የሚያደርግ በመሆኑ የመሪውን እና የድርጅቱን ጥፋቶች ማየት የማይችሉ እውሮች ስላደረጋቸው፣
- ገዥዎቹ ከተራው ሕዝብ የቀን ስቃይ የማታ ቅዠት ከተሞላው የሰቆቃ ህይወት አጅግ እርቀው፣ የየራሰቸውን የቅምጥል እና የቅንጦት ህይወት መኖር መጀመራቸው፣
- በወያኔ እና በተለጣፊዎቹ ድርጅት ውስጥ የተሰባሰበው መንጋ ብቃት፣ ችሎታ እና በራስ መተማመን በሌላቸው ግትልትሎች የተሞላ፣ አባላቱም ሆዳቸውን ከመሙላት ውጭ፣ እንደሰው ከራስ ክብር እና ከግላዊ ነጻነት የሚመነጩ ሰብአዊ ግፊቶች የማይሰማቸው መሆኑ፣
- ከዚህም በተጨማሪ፣ የተሻለ ስራም ሰሩ አልሰሩ በፖለቲካ ተቃዋሚነታቸው የመንግስት ጉድ እየዘረዘሩ ለሕዝብ በማጋለጥ፣ ከፍተኛ የስልጣን ብልግና እና የሙስና ልጓም መሆን የሚችሉ ፓርቲዎች እንዳይኖሩ መደረጋቸው እና ሌሎችንም ምክንያቶች ጨምረን የወያኔ መንግስታት እና ባለስልጣናት ስለራሳቸው ሆነ ስለመንግስታቸው፣ ሕዝብ የሚኖረውን አስተያየት እና ስሜት በምንም አይነት መንገድ ማወቅ ከማይችሉበት የህሊና እስረኛነት ውስጥ እራሳቸውን አስረው ነበር ማለት ይቻላል። የወያኔ መንግስት ባለስልጣናት በአንድ በኩል እራሳቸውን ለማየት እና ለማረም የራሳቸው ውስጣዊ ብቃት የሌላቸው በመሆኑ፣ በሌላ በኩልም እንዲታረሙና ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ የሚችሉ ከእነሱ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ነጻ ተቋማት እንዳይኖሩ በማድረጋቸው፤ «ጆሮ ለባለቤቱ ባእዳ ነው» የሚለውን ሁኔታ ፈጥረው ወደ ገደል ወረዱ።

በሃገር ላይ የፈጸሙትን ክህደት፣ የጥቅምና የህልውና ጉዳት ሕዝብ እንደ ታለቅ የሰላም እና የእድገት አቅጣጫ እና ክንውን አድርጎ እንደሚያይላቸው አድርገው እራሳቸውን ሸነገሉ። የራሳቸውን፣ የጎጥ ወገኖቻቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን የቅንጦት ህይወት የሃገሬው ሁሉ ህይወት የሚያስመሰል ለስቃይ የደነዘዘ ህሊና ፈጠሩ። ሕዝብ ሁሉ እንደነሱ በመለኪያ 1650 ብር እየከፈለ ኮኛክ ሲጠጣ የሚያድር እስከሚመስላቸው ድረስ ቀልባቸውን ስተው ከነፉ።

እነሱ በሬድዮ እና በቴሌቪዥን እንዳሻቸው ስላሽካኩ እና ስለደነፉ ሕዝብ የመናገር መብቱን ተገፎ የሚያድርበት ሃገር እንዳልሆነ አድርጎ የሚያስብ ህሊና አደለቡ:: ራሳቸውን በአመማቸው ቁጥር ፓሪስና ለንደን ለህክምና እያሉ በርካታ የውጭ ምንዛሪ ይዘው መሮጣቸው፣ ሃገሬው ጤንነቱ ተጠብቆለት የሚኖርበት ገነት በኢትዮጵያችን የሰራ የመሰለው የሚቃዥ ህሊና ፈጠሩ::

ዘረኛ የፖለቲካ ስርአት አቁመው፣ ከምኒሊክ ቤተመንግስት በየተለጣፊው ሆድ-አደር ምስለኔ የሚገዙትን ሕዝብ፣ የብሄር ብሄረሰብ መብቱን እንዳስከበሩለት አድርጎ  የሚያሳያቸውን የራሳቸውን ይሉኝታ ቢስ ህሊና አዳበሩ:: ሕዝብ እረፍት እና ፋታ የማይሰጠው የስቃይ እና የመከራ ሰውነቱ ሰለሚኖርባት ሃገር መዋረድ የተፈጸመባትን ክህደት፣ ስለራሱ መብት መረገጥ፣ ስለገዝዎቹ ሙስና፣ ዘረፋ እና ድንቁርና ሌሎችንም እኩይ እሴቶቻቸውን በልቡ ከትቦ ሊቀጣቸው አመቺ ወቅት ሲጠብቅ የነበረ መሆኑን ገዥዎቹ ፍንጭ ማየት የሚችሉ አልሆኑም::

ይህንን ሁሉ ጉድ ይዘው «እንከን የለሽ ምርጫ» አሉ:: እንዳውም አልፈው ተርፈው በቀጥታ በሚተላለፍ የምርጫ ወቅት ክርክር ለመግባት ድፍረት አገኙ:: ይህንን ማድረግ የቻሉት ራሳቸው ስለራሳቸው ያላቸውን አመለካከት የሃገሬው አመለካከት ነው የሚል በቅዠት ላይ የተመሰረተ ህሊና መላበስ በመቻላቸው ነው:: እነዚህ ጉደኞች «በሃገር ሃሳቢነታቸው፣ በአዋቂነታቸው እና በንጽህናቸው» ተማምነው የዴሞክራሲን በር ገርበብ አደረጉ:: በአሸናፊነት ትምክህት ተሞልተው ግጠሙኝ ያሉበት ሁኔታ በፖለቲካ መስኩ ፈጽሞ አልመውት፣ አስበውት የማየውቁትን ውርደት አከናነባቸው:: ወያኔን ለእዚህ የተሳሳተ ግምገማ ያበቃው ያው የተለመደ የሃገራችን ገዥዎች «ማመን የሚፈልገውን ብቻ እያጠለለ ማማን የሚችል» በሽተኛ ህሊና ይመስለኛል::

የወያኔ ገዥዎች አመለካከት፣ ለምእተ-አመታት የኖረው ሰርወ-መንግስት ከስሩ ተቦርቡሮ መውደቂያው ጠርዝ ላይ በደረሰበት ወቅት ንጉሰ ነገስት ሃይለ ስላሴ «የሚወደን እና የምንወደው ሕዝባችን» በማለት የተናገሩትን እንድናስታውስ ያሰገድደናል:: ከአስራ ሰባት አመት የስቃይ አገዛዝ በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወርቅ ሲያነጥፍ እንደከረመና ሕዝቡን ግን ፋንድያ የሚወድ ስለሆነ አመራሩን እንዳልተቀበለው አድርጎ የገለጸውንም እብሪተኛ ኮሎኔል እንዳንረሳው ያደርገናል:: ዛሬ መለስ ዜናዊና እና አደግዳጊዎቹ ደግሞ በተራቸው ማር እና ወተት ሲግቱት የኖረ ሕዝብ ያለ ይመስል በምርጫው ሽንፈት ያላበሳቸውን ሕዝብ «ውለታ ቢስ፣ ዘረኛ እና ደንቆሮ» በማለት ይሉንታ አልባ በሆነ ቋንቋ እየዘለፉት ነው:: ራሳቸውን አጽናንተው፣ ከእርሱ በላይ የሚያውቁለትን ሕዝብ በጠመንጃ እየቀጠቀጡ ወደ «ልማት እና ብልጽግና ወደ ሰላም እና መረጋጋት» እንወስደዋለን ብለው ድምጹን ረግጠው በላዩ ላይ እየጨፈሩበት ይገኛሉ:: ታሪክ ይህ መሆን እንደማይችል በቂ ማስረጃዎች ይዞ ከፊታችን ቆሟል:: ከእዚህ በላይ ከታሪክ የማይማር በሽተኛ ህሊና ከየት ያገኟል::

በአጠቃላይ የግንቦት ሰባቱ ምርጫ፣ በተለይ በወያኔ እና በተለጣፊዎቹ የገዥ መደብ አባለት ላይ ያወረደው ዱብ እዳ፣ ድንጋጤ እና ግራ መጋባት አስከትሏል:: ይህ ዱብ እዳ የሽንፈት ዱብ እዳ ነው:: በሌላ በኩልም በተቃዋሚው በኩል የማሸነፍ ዱብ እዳ ሊመጣ እንደሚችል በሚገባ ግምገማ ማድረግ እና ዱብ እዳው ለሚያመጣው መዘዝ በቂ ዝግጅት አልተደረገም:: እንዲህ አይነቱ ሁኔታ መፈጠር የቻለው፣ ፖለቲካ

ከሊሂቃኑ ክበብ ወጥቶ ክሕዝብ ጋር ባለመተሳሰሩ ነው። ልሂቁ የፖለቲካው መሰረት ከሆነው ሕዝብ ጋር ያለውን መዋቅራዊ እና ግለሰባዊ የላላ ግንኙነት የሚጠቁም ነው።

የሃገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እና የሕዝብ የለውጥ ተነሳሽነት የፖለቲካ መሪነቱን ለመስጠት ከተነሳው የፖለቲካ ልሂቅ ቀድመው በመሄድ መሪዎች ተጎታቾች የሆኑበትን ሁኔታ ሲፍጥር ዛሬ የመጀመሪው አይደለም። የ1966 የአብዮት ዘመንም እንዲህ አይነት ባህርይ ነበረው። ይህ በመሆኑም የፖለቲካ ልሂቁ እርጋታ አግኝቶ ማሰብ ባለመቻሉ በሃገሪቱ እና በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ የወታደራዊ መንግስትን አጠናክሮ እርስ በእርሱ ተናክሶ ከፖለቲካ መድረኩ የጠፋበት እና ሃገራችንንም ወያኔን ለመሰለ ዘረኛ እና አምባገነን መንግስት አሳልፈን የሰጠንበትን ሁኔታ መፍጠር ችሏል። የግንቦት 1997 ሁኔታም ሕዝብ ከፖለቲካ ልሂቁ የቀደመበት ሁኔታ ያመላከተ፣ በፖለቲካ ልሂቁ ዙሪያ ዳግም 1966ቱን ስህተቶች እንዲፈጸሙ የሚያደርግ ሁኔታ የሚያመቻች ዝንባሌዎች ታይተውበታል። ጥንቃቄ ካልተደረገ መጠላለፉ፣ መከፋፈሉ በአንድ የጋራ አላማ ስር አለመሰባሰቡ፣ ዘረኛ የሆነውን የወያኔን አምባገነናዊ አገዛዝ እድሜ የሚያራዝም፣ ሃገራዊ ውርደት እና ውድመት የሚያባብስ አደጋ ሊያከናንበን ይችላል። የሕዝብን የለውጥ ፍላጎት ጥልቀት አስቀድሞ አውቆ አለመዘጋጀት ነውር የለውም። በተለይ በእንደኛ አይነቱ አፋኝ ስርአት ባለበት፣ ሕዝብ እና የፖለቲን ልሂቃኑ በቅርበት ተገኛኝተው ለመነጋገር የሚችሉበት ሁኔታ ዝግ በሆነበት ሀገር ይህ ችግር ቢከሰት የሚያስገርም አይደለም።

ይህ ዝግጅት በቂ እንዳልነበር በሚታወቅበት ሰአት የሕዘብን የለውጥ ፍላጎት መሰረት በማድርግ ሕዝብን እና ሃገርን በማስቀደም የጎደሉትን ነገሮች በማሟላት ለመንቀሳቀስ አለመሞከር ወይም የሕዝብን መነሳሳት እኔ ካልመራሁት፣ የኔ ድርጅት ብቻ ካልተጠቀመበት በሚል መንገድ ታሪካዊ አጋጣሚ እንዲባክን ማድረግ ግን ወንጀል ነው። ወንጀል የሚያደርገው በርካታ ወገኖቻችን ከፍተኛ መስዋእትነት ከከፈሉበት የቅርብ ግዜ ታሪካችን አለመማርም ነው። ከመቼውም በላይ ወገናዊ አንድነት፣ ወገናዊ መተሳሰብ እና ፍቅር፣ ብተህውትነት፣ ሆደ ሰፊነት፣ ቀናነት እና መቻቻል የሚያስፈልግበት ወቅት አሁን ነው። በተለይ ታለቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ አመራር እንሰጣለን በማለት ከሚንቀሳቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቡድኖች እና ግለሰቦች የሚጠብቀው ይህንን ነው።

## ***<u>2- የግንቦት 7ቱ ምርጫ የሕዝብን የፖለቲካ ብስለት በማረጋገጥ ለረጅም ዘመን የሃገራችን የፖለቲካ ልሂቃን በሕዝብ ላይ የነበራቸውን ሞግዚታዊ አመለካከት ውልቅልቁን ማውጣት ችሏል፣</u>***

የግንቦቱ ምርጫ የሃገራችንን የፖለቲካ ልሂቅ ብቻ ሳይሆን በምእራብ ሃገሮች ውስጥ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀራጮችን እንደገና እንዲያስቡ የሚያስገድድ ሁኔታ ፈጥሯል። የዴሞክራሲ ጥያቄ ከማንም በላይ የደሃ ሕዝቦች ጥያቄ እንዴት መሆን እንደሚችል የግንቦቱ ምርጫ አሳይቷል። ዴሞክራሲ የሚጠቁማቸው ተስፋዎች፣ በተለይ የነጻነት እና የብልጽግና ተስፋ የሚንጠለጠልባቸው መሆኑን የተረዳ መሆኑን ሕዝብ በተግር አረጋግጧል። ለምምረጥ መመዝገብ፣ የምርጫ ካርድን በጥንቃቄ ማሰቀመጥ፣ በድለላ፣ በገንዘብ፣ ድምጽን አለማስረከብ በሁሉም ቦታዎች ታይቷል። ለጊዚያዊ ጠቀሜታ ሲባል የዘለቄታ ጥቅምን መጉዳት መሆኑን በማወቅ ሕዝብ ያሳየው ብስለት በደሃ እና ባልተማረ ሕዝብ ውስጥ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት

ግንባታ በቂ ሰብአዊ ግፊት ሊኖር አይችልም የሚለውን የሃገራችንን ሆነ የውጭ ሃገራቱን የፖለቲካ ጠበብት የቆየ መሰረተ-ቢስ ድምዳሜ ያስወገደ ሆኗል:: ሕዝብ በቀጥታ ከራሱ ህይወት፣ ካሀገሩ ህልውና እና ጥቅም ጋር በተራ ቋንቋ ያለምንም «ምሁራዊና እርእየተአለማዊ» ማጭበርበር ሊቀርቡ የሚችሉ ውይቶችን ሳይታክት ለማዳመጥ በቂ ትእግስት እንዳለው አስመስክሯል:: በመረጃ ላይ ተመስርቶ ድምጽ ሰጥቷል:: ዴሞክራሲ ለሚጠቀመው ተስፋ ሲል ብቻ የተወሳሰቡ የምርጫ አሰጣጥ ዘዴዎችን ግዜውን ወስዶ ደከመኝ ሳይል አጥንቷል:: ለምርጫው መሳካት ያደረገው ዝግጅት፣ «ዴሞክራሲ ምን እንደሆነ ይህ መሃይም ሕዝብ አያውቅም» በማለት በተግባር ባልተፈተሸ መመጻደቅ ያሙትን ሁሉ ያሳፈረ ሆኗል:: እንዲያውም የመብት ረገጣው፣ ድህነቱ እና ውርደቱ በበዛ ቁጥር አንድ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ሊያሳይ የሚችለው ፍቅር እና ቀናኢነት ጭቆናና እና ድህነት በማይታይባቸው ሀገሮች ከሚኖሩ ሕዝቦች እጅግ የላቀ እንደሚሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በተግባር አሳይቶታል:: ለእዚህም ነው ከጠዋት አስከማታ እህል ሳይቀምስ የጠዋቱ ቁር፣ የቀትር ሃሩር ሳይበግረው፣ ሀገሬው በሁሉም ቦታ እስከውድቅት ድረስ ከአውሬ ጋር እየተጋፋ በትእግስት ለሰአታት እግሩ እሰከሚንቀጠቀጥ ድረስ ቆሞ ድምጹን የሰጠው::

የወያኔ መንግስት እና የውጭ ሸሪኮቹ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው የብዙሃን ፓርቲዎች ምርጫ የዴሞክራሲ ባህል እና እውቀት ባልነበረበት ቦታ በመደረጉ ችግሮች ሊኖሩበት ይችላሉ በማለት የወያኔንን አይን ያወጣ ድምጽ ማጭበርበር ለማድበስበስ ሙከራ እያደረጉ እንደሆኑ እናውቃለን:: ወያኔ ያካሄደውን አይን ያወጣ የሕዝብ ድምጽ ዘረፋ በመካድ የምርጫውን ችግር በድፍኑ «የአዲስ ዶሞክራሲዎች ችግር ነው» በሚል ድፍን አባባል ሸፋፍኖ ለማለፍ የሚደረገው ሙከራ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሳምመውም ለእዚህ ነው:: ሕዝቡ በምርጫው ወቅት ያሳየው ብስለት እና ስነስርአት በሙሉ የሚያሳየው ሕዝብ ለዴሚክራሲያዊ ስርአት ምስረታ የሚያበቃ የእድገት ደረጃ መድረሱን ሲሆን፣ በግልባጩ ለእንዲህ አይነቱ ስርአት ምስረታ ብቃት የሌላው በስልጣን ላይ የሚገኘው ዴሞክራሲ አምጪ ተብየው የወያኔ የማፊያ መንግስት እና የእሱ የጡት አባት የሆኑት፣ ስለዴሞክራሲ እና ነጻነት የገቡትን ቃል ማክበር የማይችሉ ቀላማጅ የምእራብ መንግስታት ብቻ መሆናቸውን አረጋግጧል::

ሕዝብ በመሬት ጥያቄ፣ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ እድገት ፖሊሲ፣ በነጻ ተቋማት የመኖር አስፈላጊነት ዙሪያ የተደረጉትን ውይይቶች በሚገባ አዳምጦ መረዳት ችሏል:: በፓርቲዎች መሃከል ያለውን ልዩነት የተረዳ ምርጫ አኪያሂዷል:: ወያኔ በምርጫው ውድድር ወቅት ባሳየው ድንቁርና የሳቀው የተማረው ከተሜ ብቻ አይደለም:: ምንም አያውቅም፣ ምንም አይገባውም እና ሁሌም ሞግዚት ያስፈልገዋል ሲባል የነበረው ሰፊው የሃገሪቱ ሕዝብ ነው:: በየገጠሩ በተሰማሩ አስተማሪዎች ራድዮኖች ዙሪያ ተኮልኩሎ በወያኔ እና በተቃዋሚ-ች መሃከል ሲደረግ የነበረውን ውይይት እየሰማ በሃገሩ ገዥዎች ድንቁርና ያልሳቀ እና ያላዘነ ገበሬ በሃገሪቱ የሚገኝ አይምስለኝም:: «እነዚህ ደንቆሮዎች ነበሩ እንዴ ሲጨማለቁብን የከረሙት» በማለት ትዝብቱን ያላሰረፈ ዜጋ በሃገሪቱ የለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተለያዩ ፓርቲዎች የተለያዩ ፖሊሲዎች የደረሰበትን ግንዛቤ ዛሬም ነገም ከአእምሮው የሚፍቀው ሃይል አይኖርም::

ሕዝብ ይህንን ሁሉ ማድረግ የቻለው ለምርጫ በሚል ሰበብ በተከፈተች ትንሽ የዴሞክራሲ ቀዳዳ አማካይነት ነው:: ለአመታት የዘለቀ የፖቲካ ውይይቶች የሚደረግበት ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች እና

መሪዎች ማጥናት እና ማወቅ የሚችልበት ሰፊ እድል አግኝቶ ቢሆን ደግሞ ምን አይነት የብስለት እመርታ ማሳየት ይችል እንደነበር መገመት አስቸጋሪ አይደለም::

በዚህ ምርጫ ግፍና መከራ አምራች የሆነውን ወያኔን ለማስወገድ ሕዝብ ከፍተኛ ፍላጎት እንደነበረው ቢታወቅም ድምጹን የሰጠው ከዚህ ፍላጎት ብቻ በመነሳት፣ በፖለቲካ ድርጅቶቹ የቀረቡትን አማራጭ ፖሊሲዎች ሳያዳምጥ ነው ማለት ትልቅ ስህተት ይሆናል:: ሕዝብ ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የቀረበውን ጉዳይ በሚገባ መረዳት የቻለ፣ በአካባቢውና ከቀን ተቀን ህይወቱ ጋር ግንኙነት ባላቸው የትምህርት፣ የጤና፣ የስራ አጥነት፣ የመሰረተ-ልማት፣ የፍትህና የመሬት ችግሮች ላይ የየትኛው ፓርቲ ፖሊሲ የተሻለ እንደሆነ በሚገባ የመዘነና ጥልቀት ያለው ግንዛቤ ነበረው:: ሕዝብ ወያኔን በድምጹ የቀጣው በድፍን ጥላቻ ነው የሚሉ ዛሬም በሕዝብ ስም ወሳኝ ሆነው ለመቅረብ የሚሹ የሞግዚዊነትን የአመለካከት ቀለበት ሰብሮ በመውጣት በሕዝብ ፊት አማራጭ የሚሏቸውን ፖሊሲዎች በማቅረብ በሕዝብ ለመዳኘት ብቃቱም ድፍረቱም የሌላቸው ብቻ ናቸው:: ያም ተባለ ይህ ሕዝብ የጋራ ከሆኑ ሃገራዊ ጉዳዮች አንስቶ በየክልሉ፣ እንደ ቦታውና እና እንደ ዝንባሌው የተቃውሞ ድምጹን አሰምቷል:: በሁሉም ቦታዎች ለሁሉም ሕዝብ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች እና በየአካባቢው ደግሞ ለራሱ ግልጽ በሆኑ አጀንዳዎች ዙሪያ ግልጽ አመለካከት እንደነበረው መጠራጠር አይኖርብንም:: እንዴት እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ብስለት በሕዝብ መሃከል መገኘት ቻለ የሚል ጥያቄ አንባቢ ማንሳቱ አይቀርም:: መልሶቹ በርካታ ናቸው:: ከደርግ እና ከደርግ ዘመን በፊት ስለነበሩ ስርአቶች፣ ስለታሪካችንን እና ባህላችንን ብዙ መመራመር የሚጠይቁ ነጥቦችንም ያካትታል:: ለግዜው አንዱን እና መሰረታዊ የሆነውን ነጥብ ቀጥዬ እነሳለሁ::

## <u>3- ፖለቲካ ከሰማይ ወርዶ በእውንም ምድራዊ እና ሕዝባዊ የሆነበት ሁኔታ መፈጠሩ፣</u>

ግንቦት 97 ያሰተማረን ትልቅ ትምህርት ቢኖር የፖለቲካ ብቃት እና ብስለት ሁሌም ከሕዝብ ጋር እንደነበር ነው:: የፖለቲካ ልሂቃኑ ይህንን መረዳት ሳይችሉ የቀሩበት ዋና ምክንያት በእነሱ በሕዝቡ መሃል የመግባባት ችግር ስለነበር ብቻ ነው:: ትልቁ ችግር የፖለቲካ ቋንቋው መገናኘትን እና መቀራረብን የሚጋብዝ አለመሆኑ ነበር:: ግንቦት 97 ሕዝብ በመሬት ጥያቄ ላይ፣ በትምህርት እና በጤና ጉዳይ ላይ፣ በግለሰብ እና በብሄር-ብሄረሰብ መብቶች ዙሪያ እና በሌሎችም ገዳዮች ላይ ለመጀመሪያ ግዜ በሚገባው ቋንቋ ውይይት መስማት እና በውይይት መሳተፍ የቻለበት ነበር:: ስልጣን በፖለቲካ ልሂቃኑ መሃከል በሚደረግ ምሁራዊ ወይም የጡንቻ ፍጥጫ ሳይሆን በቀጥታ ሕዝብን በማሳመን እና የሕዝብን ድጋፍ በማግኘት የሚመጣ መሆኑ የታወቀበት ወቅት በመሆኑ፣ ልሂቃኑ ሳይወዱ በግድ የሃገሬውን ቋንቋ እየተናገሩ ስለሃገሩ ፖለቲካ ማውሳት ነበረባቸው:: ይህ በመሆኑም እንዳለፉት ዘመናት ሕዝብ በማይገባው ቋንቋ ሰለፖለቲካ አውርቶ ሕዝብ የማይመለከተውን ጉዳይ አንስቶ መሸወድ የማይቻል ነበር::

ትላልቅ እና ከባድ የቃላት እና የንድፈሃሳብ ቡቱቱቶዎችን እየጎተቱ በርእዮተ አለምና በቀኖና ስም የሚደረግ የፖለቲካ ግብግብ በግንቦቱ 97 ምርጫ ቦታ አልነበረውም:: ሕዝብ የገዛ ችግሩን ብቻ ሳይሆን የችግሮቹን መፍትሄዎች በገዛ ቋንቋው ሲነገረው ሁሉንም በሚገባ አዳምጦ እና አሰላስሎ ሚዛናዊ ፍርድ መስጠት እንደሚችል በግንቦቱ 97 ምርጫ አረጋግጦታል:: ከእዚህ በመነሳት የፖለቲካ ልሂቁ መማር የሚገባው ነገር ቢኖር ሕዝብ በማይገባው ቋንቋ ከሕዝብ ህይወት ጋር ግንኙነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ እርስ በርሱ የሚያደርገው መሻኮት ሀገራዊ ሆነ ሕዝባዊ እርባና የሌለው መሆኑ ነው:: ኢትዮጵያን

ለመቀየር የሚፈልግ የፖለቲካ ሃይል ይህንን ህልሙን እውን ማድረግ የሚችለው በቀጥታ ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ሕዝብን በማናገር እና በማሳመን ብቻ መሆኑንን ግንቦት 97 አስተምሮ አልፏል። በፖለቲካ ልሂቃኑ መሃል በባእድ ቋንቋ ይደረግ የነበረውን የፖለቲካ ቀኖና አሰጥ-አገባ ትርጉም አልባ አድርገን እንድናየው አድርጎታል።

ግንቦት 97፤ ሕዝብ አዳመጠ ፣ አሰላሰለ፣ ፍርዱን ሰጠ። መለስ ዜናዊ በጉልበት ሰብስቦ ከያዘው የዴሞክራሲ መብት ጥቂቱን ለቀቅ ባደረገበት የግንቦቱ ምርጫ ሕዝብ ድምጹን አለምን ባስገረም ስነስርአት በተሞላው መንገድ ሰጠ። ከዚህ የድምጽ መስጫ ቀን በፊት የምርጫውን ውጤት ለወያኔ የሚጠቅም ለማድረግ ብዙ ነገሮች ተደርገዋል። በገንዘብ፣ በስልጣን፣ በመንግስት ንብረት እና ሃብት ለመደለል ተሞክሯል። ይህ የማይሆን በመሰለባቸው ቦታዎች ማስፈራራት ማንገላታት፣ መደብደብ፣ ማሰርና መግደል ተካሂዷል።

ከምርጫ ቀን እና ከእዛም በኋላ ይህ ድርጊት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ሕዝብ በምርጫው በስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ በመቅጣት ድምጹን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች መስጠቱ ግልጽ የሆነባቸው የአዲስ አበባ ከተማ እና የሌሎች ከተሞች የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት ግልጽ መሆን ሲጀምር የገዥዎቹ የወያኔ መሪዎች ህሊና ከተጫነበት መደንዘዝ መንቃት ጀመረ። ከመለስ ዜናዊ በተሰጠ መመሪያ አዲስ አበባን ጨምሮ በመላው ሃገሪቱ የድምጽ ቆጠራው እንዲቆም ተደረገ። በአዲስ አበባ የምርጫ ጣቢያዎች ወያኔ በሰጣቸው መመሪያ መሰረት የወያኔ የምርጫ ታዘቢ ካድሬዎች «ምርጫው ነጻ እና ፍትሃዊ አይደለም» በሚል አስገራሚ ሰበብ ቆጠራው እንዲቆም አስደረጉ። በምርጫው ምሽት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት በቅንጅት ስም ስንከታተተል የነበርነውን ግለሰቦች ይህ ሁኔታ አስገርሞን ነበር። ምርጫ ለማጭበርበር የሚያስችል ሁሉንም መሳሪያ በእጁ ያሰባሰበው መንግስት አይን አውጥቶ «ምርጫው ነጻና ፍትሃዊ አይደለም» በማለቱ ሁላችንም ተደነቅን። ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በወያኔ አማካይነት የተሰራ ድራማ በሃገሪቱ በሙሉ የተከናወነ እንደነበር ውሎ አድሮ ግልጽ ሆኗል።

ወያኔ በሃገሪቱ በሙሉ የድምጽ ቆጠራ እንዲቆም ያደረገበት ምክንያት የድምጽ ቆጠራው ነጻ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ቢደረግ በጉልበት አፍኖ ከያዘው እና ያለተወዳዳሪ ከትግራይ ሕዝብ በአፈና ከቀማው ድምጽ በስተቀር በየትም በታ ምንም አይነት ተጨማሪ የሕዝብ ድምጽ እንደማያገኝ ስለተረዳ ነበር። የምርጫውን ቆጠራ በማስቆም ከሃገሪቱ የመወዳደሪያ ጣቢያዎች መሃከል የአለም አቀፍ ማህበረሰቡን ትኩረት የማይስቡትን እና ጠንካራ ታዛቢዎች የማይገኙባቸውን ቦታዎች ለየ። በእነዚህ ጣቢያዎች ከፍተኛ ማጭበርበር የሚቻልበትን ሁኔታ አመቻቸ። ከፍተኛ የወያኔ መንግስት ባለስልጣናት የተወዳደሩባቸው እና የአለምአቀፉን ህብረተሰብ እማኞች እና ጠንካራ የሃገር ውስጥ ታዛቢዎችን ትኩረት በሳቡ የመወዳደሪያ ጣቢያዎች የሕዝብን ድምጽ ለማጭበርበር አስቸጋሪ ስለሚሆን ቆጠራው እንዲቀጥል ተደረገ።

ታዛቢዎች ደካማ በሆኑባቸው ቦታዎች ወይም ታዛቢዎች አስቀድመው እንዳይሳተፉ የተደረገባቸውን የገጠር የምርጫ ወረዳዎች በመለየት ምርጫውን ለማጭበርበር ተወሰነ። ወያኔ ያለተቀናቃኝ በተሳተፈባቸው በትግራይና በሌሌች ጥቂት ቦታዎች ላይ በእርግጠንነት የሚያገኘውን የፓርላማ ወንበር በመደመር፣

በፓርላማ እንዲያገኝ የተፈለገውን የፓርላማ ወንበር ብዛት ከወሰነ በኋላ፣ የሕዝብ ድምጽ ዘረፋው ተጀመረ:: እሁድ ግንቦት 7 /1997 ሲነጋጋ ምረጫው አለቀ:: የሕዝብ ድምጽ ቆጠራው እንኳን ስንት ችግር ባለባቸው ገጠሮች ቀርቶ በአዲስ አበባ ተጠናቆ ባላለቀበት ማግስት ሰኞ ግንቦት 8 /1997 የወያኔ መንግስት ማሸነፉን ብቻ ሳይሆን ስንት ወንበር እንዳሸነፈ ሳይቀር በግልጽ ተናገረ:: መጪውን አምስት አመት የሚገዛው እርሱ እንደሆነ ደነገገ:: ከዘዚህ ድንጋጌ ጋር የጊዚያዊ አስቸኳይ አዋጅ አወጀ:: ሕዝብ ይህንን አይን ያወጣ የምርጫ ማጭበርበር ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ ሊቃወም የሚችልበትን እድል ዘጋ::

የድምጽ ኮሮጆዎችን በመስረቅ፣ በመቀየር፣ የሌሎች ፓርቲ ተወካዮችን አባሮ ድምጽ ቆጠርኩ በማለት፣ በግልጽ ተቆጥሮ ያበቃለትን ሰነድ ሳይቀር በመቀየር፣ ወያኔ ሰኞ እለት በመግለጫው የጠቀሰውን 327 የፓርላማ ቁጥር ለመድረስ ተግቶ መስራት ጀመረ:: ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ሃገሮች ከተማው የገጠሩን አመለካከት እንደሚገዛው እየታወቀ ወያኔ በከተማ ዜሮ ሲወጣ ከከተማው ብዙ ርቀት በሌላቸው ገጠሮች «ተቃዋሚዎቼን ዜሮ አወጣኋቸው» ማለት ቀጠለ:: በየገጠሩ ለምርጫ ያቀረባቸው ከፍተኛ ሚኒስትሮቹ ጠንካራ የምርጫ ታዛቢ ስለገጠማቸውና ማጭበርበር ስላልቻሉ እጅግ አሳፋሪ በሆነ ውጤት ሲሸነፉ፣ እዚያው ከጎናቸው በነበሩ ሌሎች የገጠር የምርጫ ጣቢያዎች እዚህ ግባ የማይባል፣ በሕዝብ ላይ ስንት በደል ሲፈጽም የነበረ ወንጀለኛ ካድሬ ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮችን በከፍተኛ ድምጽ አሸነፈ ይባል ጀመር:: ለምን እና እንዴት እነበረከት ሰምኦን፣ እነ ጁነዲን ሰዶ እነ አባዱላ እነ አቶ ሃርቆየ የመሳሰሉ አውቅ የወያኔ ባለስልጣናት በተሸነፉባቸው አጎራባች የገጠር የምርጫ ጣቢያዎች አንድ ተራ የወያኔ ካድሬ ማሸነፍ እንደቻለ ለማወቅ ሕዝብ ጠንቋይ መቀለብ አልነበረበትም:: በጣም የሚገርመው ከሶስት ወር በላይ የፈጀው የምርጫ ቆጠራ ተጠናቆ፣ ውጤት በምርጫ ቦርድ ሲገለጽ ወያኔ ያገኘው የፓርላማ ወንበር ብዛት ያው መለስ ዜናዊ ገና ቆጠራው ሳይጀመር አሸንፍያለሁ ብሎ ከተደነገገው ወንበር አንዲት ወንበር ዝቅ ወይም ከፍ አለማለቱ ነው:: ምርጫ ቦርዱም ወያኔ ያሸነፈው የወንበር ብዛት 327 ነው በሎ አረፈው:: ሌብነትም አይነት አለው ይህ ደግሞ ከአይንም አይን ያወጣው ነው::

ሕዝብ ስለ ዴሚክራሲ ምንነት ማወቅ ሳይቸግረው፣ ስለ ዴሞክራሲያዊ የአመራረጥ ቴክኒክ ብዙ ግራ ሳይጋባ፣ አውጥቶ አውርዶ ተጨንቆ ተጠቦ የሰጠውን ድምጽ ተዘረፈ:: መብቴ ይከበር ብሎ ሲነሳ ተጨፈጨፈ:: የሕዝብ ድምጽ ይከበር ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በፍርድ ቤት እና በምርጫ ቦርድ አማካይነት ፍትህ ጠየቁ:: ፍርድ ቤቱ እና ምርጫ ቦርዱ ግን አይን ባወጣ መንገድ ለፈጣሪያቸው ለወያኔ የሚጠቅም ውሳኔ ወሰኑ:: እንዲያውም የወያኔን «እስቲ ምን እደርጉኛላችሁ» የሚል መልእክት ማስተላለፊያ ቱቦዎች ሆነው አረፉት:: አልፎ ተርፎ፣ ምርጫ ቦርዱ ማጭበርበሩን ያኪያሄዱት ተቃዋሚዎች ናቸው ብሎ አረፈው:: ተቃዋሚዎች ተጭበርብረናል ይጣራልን ያሉባቸውን የምርጫ ውጤቶች መጭበርበር ያልተካሄደባቸው ናቸው በማለት ወሰነ:: ወያኔ አይን አውጥቶ ተጭበርብሬአለሁ ያለባቸውን 75 የምርጫ ጣቢያዎች «አዎን ተጭበርብረዋል» በማለት የማጣራት ሂደቱን ያከናወነው የምርጫ ቦርድ እና የወያኔ ግንባር በሁለት ለአንድ ድምጽ የተቃዋሚዎችን የፍትህ ጥያቄ እየረገጡ ወሰኑት:: በዚህ ውሳኔ መሰረትም ሕዝብ በድፍረት እና በቆራጥነት በምርጫው የቀጣቸውን የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በድጋሚ የሚመረጡበትን ሁኔታ ተመቻቸ:: ሁላችንም እንደምናውቀው:: የማስታወቂያ ምኒስትሩ፣ የኦሮሚያው ፕሬዚደንት፣ የመከላከያው ሚኒስትር፣ የፍትህ ሚኒስትሩ ሌሎች በመጀመሪያው ምርጫ በግልጽ በሕዝብ የምርጫ ድምጽ የተቀጡት እና የተሸነፉት ደናቁርት ገዢዎች እንደገና ምርጫ

እንዲደረግላቸው ተወሰነ። ይህ የተገመደለ ፍረድ ያስቆጣቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ሕዝብ ባልተሳተፉበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች እንደገና ተወዳድረን አሸንፈናል በማለት ያለምንም ሃፍረት ፓርላማ ገቡ።

ሕዝብ ከማርጫው በፊት፣ በምርጫው ወቅት እና ከእዛም በኋላ በነበሩት ጥቂት ወራት የተፈጸመውን በሙሉ በአንክሮ አጤነ። ይህ ጥናት ከራሱ የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅስቃሴ እና ተመክሮ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ብዙ አመት ሊፈጅበት ይችል የነበረውን የፖለቲካ እውቀት በአጭር ግዜ ውስጥ ለመገብየት ቻለ። ይህ እውቀት መሰረታዊ በመሆኑ የወደፊቱ የሃገራችን እና የሕዝባችን የዴሚክራሲ እና የነጻነት ተስፋ መሰረት ነው፣ ብንለው ማጋነን አይሆንም። ይህ እውቀት የበርካታ ግንዛቤዎች ድምር ውጤት በመሆኑ ዋና ዋናዎቹን ዘርዘር አደርጎ ማየቱ ጠቀሜታ አለው።

ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ስለመሆኑ በሃገራችን «ስልጣን የሕዝብ ነው» የሚለውን አባባል እንኳን ሕዝቡ ቀርቶ ይህንን አባባል አምራች የሆነውም የፖለቲካ ልሂቅ የሚያምንበት ነበር ማለት አይቻልም። በሕዝብ ስም ሕዝብን ሳያመክሩና ሳያሳትፉ በተለመደው ሞግዚታዊ አመለካከት ለሕዝብ የሚበጀውን እና ከሕዝብ በላይ እናውቃለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲናከሱ የኖሩበት ሃገር መሆኑ ብቻ ለእዚህ ማስረጃ ነው። እስቲ ወደ ሕዝቡ እንሂድና ይህ በስሙ የምንምልለት እና የምንገዘትለት ሕዝብ የሚለንን እንስማ ወይም ይፍረደን፣ የሚል ቋንቋ ያለተለመደ እንደሆነ እናውቃለን። እንደእውነቱ ከሆነ ከፖለቲካ ልሂቁ መሃከልም በችሎታ እና በብቃቱ ስልጣን መያዝ ይገባኛል፣ ይጌም አርባና ያለው ነገር ለሃገር እና ለወገን እሰራብታለሁ ብሎ በራስ መተማመን ላይ በመቆም ለስልጣን መያዝ የተንቀሳቀሰ መኖሩ ያጠራጥራል። የግንቦት 1997 ምርጫ ግን ሕዝብም ሆነ በፖለቲካ ልሂቃኑ ዘንድ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ የታየበት ሆኗል። የፖለቲካ ልሂቃኑን ጉዳይ ለግዜው እንተወው እና በሕዝብ ዘንድ የተከሰተውን የአመለካከት ለውጥ እንመልከት።

ከምርጫው በፊት በተቃዋሚ ፓርቲዎች እና በወያኔ ፓርቲ ይደረጉ የነበሩ ቅስቀሳዎች ሕዝብን የፖለቲካ ስልጣን ምንጭ በማድረግ ሕዝብን በመማጸን ድምጹን እንዲሰጣቸው የጠየቁ ነበሩ። የእነዚህ ቅስቀሳዎች ብዘት እና ጥንካሬ ሕዝብ እራሱን፣ እውን የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነኝ እንዴ? አውንስ በእዚች የምርጫ ካርድ አማካይነት ሹም ሽር ማድረግ እችላለሁ እንዴ? በማለት ጥያቄ እንዲያነሳ አድርጎታል። ወትሮም ቢሆን እንደ እርሱ ሰው የሆነ ሰው ሲረግጠው እና ሲዘርፈው ትክክል አለመሆኑን ነፍሱ ስትነግረው የኖረ ሕዝብ የሃብት እና የስልጣን ምንጭ መሆኑን ለመረዳት የሚያስፈልገው ትንሽ ግፊት ብቻ ነበር። የምርጫው ቅስቀሳ ይህን ግፊት ፈጥሯል። ምርጫውን በሚመለከት የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት እና መንግስታዊ ያለሆኑ በርካታ ድርጅቶች የሰጡት ትምህርት እና ያስተላለፉት ማስታወቂያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን እንዲረዳ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ከእዚህ በተጨማሪ ሕዝብ ታላላቅ ናቸው ብሎ የሚያስባቸው ግለሰቦች ከሞቁ የከተማ ቤቶቻቸው ተነስተው በየገጠሩ እየወረዱ ሲማጸኑት፣ የመንግስትም ከፍተኛ ካድሬዎችም እንዳሻቸው ከሚያዙበት የመንግስት ገንዘብ እየቆነጠሩ ሲረጩለት፣ ብትን ጨርቅ ሳይቀር ከሰማይ በሄሊኮፕተር ሲጥሉለት (ወላይታ ውስጥ የተደረገ) እና ሰንጋ እያረዱ ግብር ሲያስገቡለት፣ እባክህን በምርጫው ቀን አትርሳን እያሉ ሲለምኑት

የተመለከተ ሕዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን መረዳት ችሏል፡፡ በእዚህ ጉዳይ ሕዝብ ግልጽ እየሆነ በመጣበት የምርጫ ወቅት ምን ያህል በልበ-ሙሉነት እና በራስ መተማን የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችን ያነጋግር እንደነበር በየገጠሩ በተደረጉ የቅድመ ምርጫ እንቅስቃሴዎች ለመታዘብ የቻልነው ሁሉ እናስታውሰዋለን፡፡

1966 ስልጣናችንን ከሰማያት ሰማያት በመጣ የፈጣሪ ምርጫ ያገኘነው ነው ሲሉ የነበሩትን የነገስታት ዘመነ መንግስት አስወግዶ፣ ስልጣን በምድር እንደማንኛውም ትል የሚርመሰመሱ ሰዎች ሊይዙት የሚችሉት ነገር እንደሆነ ያረጋጋጠ ነበር፡፡ ይሁንና በወቅቱ ስልጣን የሕዝብ ነው ይባል እንጂ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ አምሮ የተነሳ የፖለቲካ ልሂቅም፣ የፖለቲካ አመለካከትም በሃገሪቱ አልነበረም፡፡

ግንባር ቀደም መሪ ድርጅቶቹ እንደ በግ የሚያዩትን ሕዝብ በአሻቸው መንገድ ለመምራት ስልጣናቸውን በሕዝብ ስም እንደያዙት ቢደሰኩርም እውነቱ ግን ስልጣን ሕዝብ የተገኛኙበት ሁኔታ ከቶውኑ አልነበረም፡፡ ስልጣን የሕዝብ ነው የሚለው አባባል ራሱ ከሕዝብ ህይወት እና ህሊና እርቆ የፖለቲከ ልሂቃኑ ሰማይ ሰማያት ላይ የርእዮተ አለም ጨዋታ የሚጫወቱበት እረቂቅ የሃሳብ ኳስ ነበር ማለት ይቻላል፡፡
ግንቦት 97 የከፈተው ጠባብ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ስልጣን የሕዝብ ነው፣ የሚለውን አባባል ከተንጠለጠለበት ሰማይ አውርዶ ከሕዝብ ህይወት እና ህሊና ውስጥ ጨመረው፡፡ ከአሁን በኋላ ይህ ስልጣን የሕዝብ ነው የሚለውን አመለካከት ከሕዝብ አይምሮ መፋቅ አይቻልም፡፡ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት እና የአምባገነንነት ስርአት ሞት የማይቀር መሆኑን ከሚያደርጉት ነጥቦች አንዱ የግንቦቱ ሰላማዊ አብዮት በሕዝብ ህሊና ውስጥ የፈጠረው፣ ሕዝብ የስልጣን ምንጭ ባለቤትነቱን ያወቀበት እና ያረጋገጠበት ሁኔታ መከሰቱ ነው፡፡

ፖለቲካ በሕዝብ ቋንቋ መነገሩ የሕዝብ የፖለቲካ ብቃት ሕዝብ በስልጣን ምንጭነቱ የዳበረ ግንዛቤ ላይ ቆሞ በፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል ያለውን የፖሊሲ ልዩነት፣ አዎን የፖሊሲ ልዩነት አዳምጦ ልዩነታቸውን ለመረዳት ያቻለበት ሁኔታ በሕዝብ ላይ ታላቅ በራስ የመተማመንን ስሜት ፈጥሯል፡፡ ግንቦት 1997 ሌላው መለያው ፖለቲካ በቀጥታ ከሕዝብ የቀን ተቀን ህይወት ጋር ትስስር ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚሽከረከር ማህበራዊ እውነታ መሆኑን በግልጽ ያሳየ መሆኑ ነው፡፡ የሚወራውና የሚተነተነው የተለያዩ የኮምኒስት ጎራዎች የርእዮተ አለም ንጽጽሮሽ አልነበረም፡፡

ፖለቲካ፣ የኢትዮጵያ ገበሬ ስማቸውን መድገም የማይችላቸውን የውጭ ዜጎች እየጠቀሱ ሰምቷቸው የማያውቃቸውን ቃላትና ንድፈሃሳባት እየተወራወሩ ሕዝብን ግራ የሚያጋቡበት ማህበራዊ እውነታ መሆን እንደሌለበት ሕዝብ ማየት የቻለበት ሁኔታ ግንቦት 97 ይዞ መምጣት ችሏል፡፡ ውይይቱ በመሬቱ፣ በልጆቹ ትምህርት፣ በስራ አጥነት፣ በጤና፣ በመሰረተ ልማት በመኖሪያ ቤት ችግር፣ በሙስና፣ በአድሎኛነት፣ በፍትህ፣ በሃገር ጥቅም ክብር እና ደህንንነት ዙሪያ ሕዝብ በሚገባው ተራ ቃላት እና ቋንቋ የሚደረግ በመሆኑ ወይይቱን ለመረዳት ልዩ ችሎታ የሚጠይቅ አልነበረም፡፡ ለመጀመሪያ ግዜ ፖለቲካ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በአይኑ የሚያየው በጆሮው የሚሰማው የሚያሸተው እና የሚቀምሰወ ቀላል ነገር እንደሆነ የተረዳበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በተለይ ይህ ግንዛቤ ሰፊው የሃገሬው አርሶ አደር ለፖለቲካ ትልቅ ትርጉም እንዲሰጥ አድርጎታል፡፡ የፖለቲካ ለውጥ በማምጣት ሁለንተናዊ የመከራ ህይወትህን መቀየር ይቻላል በማለት ሊቀርቡት የሚፈልጉትን የለውጥ ሃይሎች አትጠጉኝ የሚልበትን የፍራቻ እስርቤት ሰብሮ

መውጣት እንዲችል አብቅቶታል። በሃገራችን ታሪክ አርሶ አደር ለመጀመሪያ ግዜ የፖለቲካ ድርጅቶችን «ኑልን፣ ኑና አናግሩን » ያለበት፣ ከምርጫው በኋላም ድምጹ መጭበርበሩ ሲያውቅ መልእክተኞቹን በመላክ «ድምጻችንን ለማስከብር እንድችል አመራር ስጡን እኛ ለምንሞተው እና ምን አስፈራቸሁ» (ከጎንደር እና ከጎጃም ገበሬ የላካቸው መልእክተኞች) የሚል ፈታኝ መልእክት ለቅንጅት አመራር እስከመላክ የደረሰበትን ሁኔታ ፈጥሯል።

በሌላ በኩል ከአሁን በኋላ የሃገሬውን የህይወት ችግሮች በሚገባ ሳያውቁ፣ ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ እነዚህን ችግሮች ዘርዝረው ሳያስቀምጡ፣ ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ መፍትሄያቸውን ሳይጠቁሙ በሕዝብ መሃል የፖለቲካ ድርጅት ነን በማለት መንቀሳቀስ የማይቻል መሆኑን ምርጫ 97 ግልጽ አድርጎታል። በቃላት ጋጋታ እና በፕሮፓጋንዳ ታጥሮ ሕዝብ በማይገባው ቋንቋ እየተናገሩ በፖለቲካ ድርጅትነት መቀጠል የማይቻል ሆኗል። ከአሁን በኋላ ፖለቲካ ሃገራዊ በሆነ ትልቅ የጥናት እና የምርምር አቅም የተደገፈ፣ የሕዝብን ህይወት በሚመለከት ዝርዝር እውቀት ያለው ማህበራዊ እንቅስቃሴ እንጂ ከእዚህ ቀደም እንደሚደረገው የውጪ ሃገራትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራም በመቃረም እና በመኮረጅ ሊከናወን የማይችል ተግባር እንደሆነ መታወቅ አለበት።

## *4 ግንቦት 97 እና የሕዝብ ድምጽ መጭበርበር ያስከተለው ታላቅ የፖለቲካ ግንዛቤ፣*

ሕዝብ እያንገራገረም፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች እየተቀሰቀሰ እና እየተለመነም የምርጫካርዱን በእጁ አገባ። በገዥው ፓርቲና እና በተቃዋሚ-ች መሃከል የሚኪያሄደውን ክርክር አዳመጠ። የሚሰጠውን ቅስቀሳ በጥሞና ሰማ። የምርጫ ቀን ሲደርስ በጥንቃቄ ያስቀመጣትን ካርዱን በአግባቡ ተጠቀመባት። በገንዘብ የደለሉትን፣ ደግሰው ያበሉትን፣ ግብር እንምርሃለን፣ ወርቅ እናለብስሃለን ያሉትን ቀላማጅ የወያኔ ባለስልጣናት ሳይሆን ምንም ስልጣን የሌላቸውን፣ በቃል የሰጡትን ተስፋ በተግባር ይተረጉሙት እንደሆን ለመፈተን ብሎ ለተቃዋሚዎች ድምጹን ሰጣቸው። ሕዝቡ ይህንን ሲያደርግ ግን በወያኔ የስልጣን ሱሰኛነት ላይ ትልቅ ስጋት እንዳለው ደጋግሞ እየገለጸ ነበር። «ድምጹንስ እንሰጣችኋለን ነገር ግን እንዴት ሆኖ ነው ይሄ ብዙ የለመደ አስከፕርሱ የታጠቀ የማጅራት መችዎች መንግስት በሰላም ስልጣን ይለቃል» የምትሉን በማለት ደጋግሞ ጠይቋል (የወሎ አርሶ አደር)። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ትልቁ የመከራከሪያ ነጥብ «ግድ የለህም መጀመሪያ አንተ ድምጽህን ስጠንና እኛ እናሸንፍ፣ ከእዛ በኋላ የቀረውን ደግሞ በጋራ እንጨነቅበታለን» የሚል ነበር። «ወያኔ እራሱ እንወዳደር ብሎ ባመጣው የምርጫ ጨዋታ ተሸንፎ ስልጣን አለቅም» ማለት አይችልም። የወጭም ጌቶቹም አይፈቅዱለትም» በሚል መግለጫ ነበር የሕዝብን ጥርጣሬ ለማርገብ ሙከራ ይደረግ የነበረው። ይህ ይባል እንጂ ሕዝብ በመሰረቱ ተቃዋሚውን ለስልጣን የሚያበቃ ድምጽ ሰጥቶ የተፈራው መፋጠጥ ከመንግስት ጋር ሊፈጠር ይችላል ብለው ያሰቡ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።

ሕዝብ ከምርጫው በፊትም የታዘባቸው በርካታ ነገሮች ነበሩ። ገዥው ፓርቲ የመንግስት ገንዘብ፣ መኪና፣ የመንግስትን ሰራተኞችን ሌሎችንም አግባብብ ያልሆኑ መሳሪያዎች ለምርጫው ሲጠቀም አይቷል። ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ከተሰጠው ጥቂት ደቂቃወች ጋር ሲወዳደር መንግስት ቀንና ሌሊት የሬድዮና እና የቴሌቪዥን ጊዜ በመጠቀም የፓርቲውን ፕሮፓጋንዳ ሲያኪያሂድበት አድምጧል። በምርጫ ቦርድ እና የምርጫ ቦርድ በምርጫ አስፈጻሚነት ያቋቋማቸው፣ በየምርጫ ወረዳ የሚገኙ ኮሚቴዎች ውስጥ የተሰገሰጉት ግለሰቦች አብዛኛዎቹ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች እንደሆኑ ታዝቧል። ከእዚህም አልፎ ወያኔ

ያለመመረጡን አደጋ ባየባቸው ገጠሮች ወታደሩን እየላከ ሕዝብን ሲያስፈራራ፣ ሰያንገላታ እና ሲገድል እንደነበር አይቷል። ሕዝብ ሁሉንም ነገር ደምሮ የመወዳደሪያው እድል ሚዛኑ እንዲህ ለወያኔ እንዲያደላ በተደረገበት ምርጫ እንዴት ነው ማሸነፍ የሚቻለው በማለት ደጋግሞ ጥያቄ አቅርቧል። ለእዚህ ጥያቄ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በቂ መልስ ባይኖራቸውም፣ ይህን አይነቱ የሕዝብ ጭንቀት በአደባባይ ለውይይት የቀረበባቸውን መድረኮች በመፍጠር የየአንዳንዱ ግለሰብ ጭንቀት ከሌለው ወገኑ ጭንቀት ጋር አንድ አይነት እንደሆነ እንዲረዳ እና የጋራ መፍትሄ እንዲፈለግለት ማድረግ ችለዋል።

እንዲህ አይነቱ መድረክ ግሰቦች በወያኔ ላይ ያላቸውን ምሬት በአደባባይ የገለጹበት፣ ይህም ተመሳሳይ ምሬት ከአላቸው ወገኖቻቸው ጋር በስሜት የተቆራኙበት ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ቁጥራቸውም ከወያኔ አጨብጫቢዎች የበዛ መሆኑን የተረዱበት እና ሁሉም በስነስርአት ድምጻቸው ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢሰጡ ወያኔ ከነጠመንጃው፣ ከነመደለያው ገንዘቡ፣ ከጠዋት እስከማታ ቱልቱላውን ከሚነፋበት የራድዮ እና የቴለቪዥን ጣቢያዎቹ ጋር ውርደት እንዲከናነብ ማድርግ እንደሚችሉ የልብ ልብ ሰጥቷቸዋል። እያንዳንዷ ድምጽ ተደምራ ወያኔን ሽንፈት ማላበስ ይቻላል የሚል የሕዝብ እምነት፣ የአንድ ሰው የምርጫ ካርድ እንዳይባክን ለማድረግ ባስቻለው ጥረት ተገልጧል። የአንድ ሰው ድምጽ ምን ትርጉም አለው በማለት ላለመምረጥ የዳዳቸውን ግለሰቦች ሕዝብ እያስጨነቀ ከምርጫው እንዳይቀሩ አድርጓል። ድንገት የእኔ ድምጽ ቀርታ ወያኔ በወረዳዬ በአንድ ድምጽ ቢያሸንፍስ የሚል ስጋት የገጠማቸው፣በእርጅና እና በህምም አልጋ ላይ ውለው የነበሩ ደካሞች፣ የሰርግ በአል የነበራቸው ሙሽሮች፣ የንግድ ስራቸውን ጥለው ቀኑን ሙሉ መሰለፍ ትልቅ የገንዘብ ኪሳራ የሚያስከትልባቸው የግል ተዳዳሪዎች እና ሌሎችም በርካታ ፈተና የነበረባቸው ግለሰቦች የገጠማቸውን ፈተና እያለፉ ድምጻቸውን ሰጥተዋል። ሕዝብ፣ የምርጫ ካርድን ትርጉም ያየበት እና ሰው ደምጹን ከፍተኛ ትርጉም እዳለው በመገንዘብ ያደረገው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ዝርዝሩ የማያልቅ ነው። የዝርዝሩ መቋጫ ግን አንድ ብቻ ሆነ። በድፍረት እና በራስ መተማመን በብዛት ወደ ምርጫው ጣቢያ በመሄድ ወያኔን በከፍተኛ ደረጃ ያዋረደ እጅግ ዝቅተኛ ድምጽ እንዲያገኝ አድርጎ ክፉኛ ቀጥቶታል። እንዲህም ሆኖ ይህ እያንዳንዱ ዜጋ በብዘት እና በከፍተኛ ንቃት የተሳተፈበት ምርጫ የገኘው ፓርቲ ጉልበትን፣ ስልጣንን፣ ሃብትን፣ ራድዮውን እና ቴሌቪዥኑን በሞኖፖል በተቆጣጠረበት ሁኔታ የተካሄደ በመሆኑ መራጩ ስጋት አልነበረውም ማለት አይደለም። በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ በፖለቲካ ፓርቲዎች መሀከል የሚደረግ የፖለቲካ ውድድር ከቶውኑ ነጻ እና ፍትሃዊ ሊሆን እንደማይችል በተግባር የተማረበትን ሁኔታ ፈጥሮለታል።

ሕዝብ፣ የገኘውን ፓርቲ በሚጠቅም መንገድ በተዘጋጀ የምርጫ ሁኔታ ውድድር ለማድረግ ወስነው በድፍረት በምርጫው ለተሳተፉት የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሰጠው ድምጽ ሲጭበረበር ተመለከተ። ይህንንም ማጭበርበር ለማስቆም እርሱና የመረጣቸው ፓርቲዎች የገጠማቸውን ችግር አጤነ። በእዚህ ጥናት ሕዝብ የደረሰበት ግንዘቤ ነው ታላቁ የግንቦቱ የፖለቲካ ትምህርት። አሁን ላለንበት አጠቃላይ ሃገራዊ ፖለቲካ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ይህ ግንዛቤ ነው።

ለዘመናት፣ በተለይ ደግሞ ላለፉት 14 አመታት በሃገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ የሚገኘው የሃገራችን የፖለቲካ ልሂቅ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መኖር የነጻ የመንግስት እና የሲቪል ተቋማት መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ሲወተውት እንደነበር እናውቃለን። ይህ ውትወታ ከአንገት በላይ ይሁን ከልብ የታመነበት፣

የተነሳው ነጥብ በእውነታነቱ አጠያየቂ አልነበረም። የነጻ ተቋማት አስፈላጊነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተወስኦ (discourse) ውስጥ ታላቅ ቦታ የያዘበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ነጻ ተቋማት የሚለውን ስንኝ እንደ ውዳሴ መድገም ከጀመርን ሰንብተናል።

ከምርጫው በፊት በህብረቱ በኩል የቀረበው ሃሳብ ያለነጻ ተቋማት መኖር፣ ምርጫ ትርጉም እና ውጤት አይኖረውም የሚል እንደነበር እናውቃለን። እንዲያውም ሌላው ቀርቶ ከእነዚህ የነጻ ተቋማት መሃል «የምርጫ ቦርዱ ከገዢው ፓርቲ ነጻ የሚሆንበት ሁኔታ ሳይረጋገጥ ምርጫ አንገባም» ተብሎ እንደነበር ግልጽ ነው። አሁን በሃገራችን የተፈጠረው ሁኔታ ህብረቱ ከምርጫው በፊት ለነጻ ተቋማት መኖር የሰጠውን ትኩረት የበለጠ ያጎላው ሆኗል። በሌላ በኩልም በቅንጅት በኩል የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች በነጻ ተቋማት አስፈላጊነት ጉዳይ ላይ ከህብረቱ የተለየ አቋም አልነበራቸውም። ልዩነቱ የወያኔን መንግስት ይህንን የተቃዋሚዎች ጥያቄ የማስተናገድ ፍላጎት የሌለው መሆኑና «ይህንን የወያኔን ፍላጎት ማጣት ለማስቀየር የሚያስችል ሕዝባዊ ግፊት ለማድረግ አቅሙም ዝግጅቱን ባለመኖሩ ምርጫውን በነጻ ተቋማት ያለመኖር ምክንያት ሳይሳተፉ መቅረት የበለጠ ጉዳት ያስከትላል» የሚል ብቻ ነው። የቅንጅት እምነት ምርጫው በሚሰጠው ጠባብ ቀዳዳ በመጠቀም ሕዝብን በመድረስ እና በመቀስቀስ ከቀድሞው የበለጠ ሰው በፓርላማ ማስገባት ከተቻለ በሃገሪቱ እየተስፋፋ የመጣውን የተስፋ መቁረጡን ሂደት ማስቆም ይቻላል የሚል ነበር።

ዛሬ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አውታር የሆኑት ነጻ ተቋማት ከሌሉ ምርጫ ውስጥ አንገባም ብለው ለመወሰን ጥቂት ቀርቷቸው ከነበሩት እና በምርጫው የተወዳደሩት ሁለቱ የህብረቱ አባል የነበሩ ድርጅቶች ፓርላማ ገብተዋል። በሌላ በኩል ያለምንም የነጻ ተቋማት ምስረታ ምርጫ ውስጥ የገባው ቅንጅት ፓርላማ ለመግባት የነጻ ተቋማትን ጥያቄ በቅድሚያ ሁኔታነት በማንሳት መሪዎቹ እስር ቤት የገቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ይህንን የተገለባበጠ እውነታ የፈጠሩት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ለእዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ቀላል አይደለም። ከግለሰብ፣ ከቡድን ማንነት እና ምንነት ጋር ከተያያዙ ምክንያቶች አንስተን ከግለሰቦች ከቡድኖች ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ግለሰቦችን ሕዝብን እና ሃገርን መቅረጽ ከሚችሉ ታላለቅ ኩነቶች ጋር እያዛመድ መግለጽ ይቻላል። ለእዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የእዙህ ጽሁፍ አላማ ስላልሆነ አንባቢን ቢያስዘንውም አንጠልጥዬ እተወዋለሁ። ይሁን እና በእዚህ ጽሁፍ ማእቀፍ ውስጥ የነጻ ተቋማት ጥያቄ ከፖለቲካ ልሂቁና ከፖለቲካ ድርጅቶቹ አልፎ እንዴት የተራው ገበሬ ጥያቄ እንደሆነ ማየቱ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት በሚለው ጉዳይና ለመመስረትም ምን መሟላት ይገባዋል በሚለው ጥያቄ ላይ እንደ ዘንድሮ በቂ እውቀት የቀሰመበት የታሪክ አጋጣሚ አግኝቶ አያውቅም። መረጠ፣ ድምጹ ተጭበረበረ። ለምን ድምጼ ይጭበረበራል አለ። አዎን ለምን የሕዝብ ድምጽ ይጭበረበራል ብለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠየቁ። የሕዝብ ድምጽ ይከበር አሉ። ወያኔ ግን ወታደሩን፣ ድህንነቱን እና ፖሊሱን ተማምኖ «ማን ወንድ ይጠይቀኛል» አለ። እንዳሻው በሚያዝበት የመገኛኛ ብዙሃን ሕዝብ ድምጹን በሰጣቸው መሪዎቹ እና በራሱ በሕዝቡ ላይ የስድብ፣ የማስፈራራት እና የድንፋታ ዶፍ ማውረዱን ተያያዘው። ማሰር እና መግደል ብቻ ሆነ ስራው። ሕዝብ ድምጽ እንዳይጭበረበር ዳኝነት ይቆማሉ ብሎ

ወደ አሰባቸው የምርጫ ቦርድ እና የፍርድ ቤት ዳኞች አቤቱታውን ይዞ ሄደ:: እነዚህ ለይስሙላ የቆሙ፣ በወያኔ ቅጥረኞች የተሞሉ ተቋሞች በመሆናቸው፣ ፍትህ ማግኘት አልተቻለም:: በአንድ ተአምር ፍትህ መስጠት ችለው ቢሆንም የፍትህ ውሳኔ ማስፈጸም የሚችሉት የፖሊስ እና የጦር ሃይል አካለት በወያኔ ፍጹማዊ ቁጥጥር ስር በመሆናቸው ተፈጻሚነት አይኖረውም ነበር:: ከምርጫው በኋላ የሆነው ሁሉ ባጠቃላይ ሲታይ ሕዝብ ከምርጫው በፊት ጠርጥሮት የነበረው ነገር እውን እየሆነ መምጣቱን ያረጋግጣል:: «መምረጡንስ እንመርጣችኋለን ግን ወያኔ ቢሸነፍ በሰላም ከስልጣን የሚወርድ ይመስላችኋል?» የሚለው ጥያቄ ለቀልድ ያልቀረበ ጥያቄ እንደነበር ግልጽ ሆነ:: ሕዝብ ከመሪዎች ለመቅደሙ አንድ ማስረጃ ሆነ::

ድምጹን ለማሰከበር አስከመሞት የሚደርሱ የተለያዩ ሙከራቸው ያደረገው ሕዝብ ለመጀመሪያ ግዜ ስለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት እና የዴሞክራሲ ስርአትን እውን ለማድረግ ስሚያስችሉ የነጻ ተቋማት ምስረታ ግንኙነት በቀጥታ ከራሱ ተመክሮ ተማረ:: የሃገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃን ለረጅም ዘመናት ሲጮሁለት የነበረው፣ ህብረትም ከምርጫው በፊት አንስቶት የነበረው የደሞክራሲያዊ ተቋማት አስፈላጊነት ጥያቄ ለሕዝብ ፍንትው ብሎ ታየው:: ይህንን ማድረግ የተቻለው ግን ቅንጅት ምርጫው እንሳተፍ በማለት በወሰደው እርምጃ እና ሁሉም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪል ማህበራት ሕዝቡ በስፋት እንዲመዘገብ ተመዝግቦ እንዲመርጥ ባደረጉት የጋራ ጥረት እና በምረጫው ወቅት ሕዝብን ለማንቃት በሰጡት ትምህርት ነው:: ሕዝብ ሺ ግዜ የምርጫ ካርድ ቢያወጣ፣ ሺህ አመት በፓርቲዎች መካከል የሚደረገውን ክርክር ቢያዳምጥ፣ 15 ሰአታት ሳይሆን 51 ሰአታትም በየምርጫው ጣቢያው ያለ ምግብ እና ወሃ፣ እግሩ እስከሚያልቅ ቆሞ ቢመርጥም፣ ድምጹን በአግባቡ የሚቆጥሩ አካላት ከሌሉ፣ እነዚህ አካለት በአግባቡ የቆጠሩትን ድምጽ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲቀበሉ፣ እምቢም ካሉ ብይን የሚሰጥ ዳኛ እና ፍርድ ቤት ከሌለ፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ ማስፈጸም የሚችል የፖሊስ ሃይል ካልተፈጠረ፣ ጉዳዩ ከእዘህ ካለፈም፣ ፖሊሱን የሚያግዝ ነጻ እና ለህገ-መንግስት ብቻ ተገዥ የሆነ የመከላከያ ሃይል ካልተመሰረተ፣ ምርጫ ዴሞክራሲ የሚሏቸው ነገሮች ያአምባገነንነትን ክረፋት ለመሸፈን የተፈጠሩ ሽቶዎች ብቻ ሆነው እንደሚቀሩ ግንቦት 97 ለሕዝብ ታላቅ ግንዛቤ አስጨብጧል:: ይህ ግንዛቤ የግንቦት 97 ታለቁ የፖለቲካ ድል ተብሉ ሊጠቀስ ይገባዋል::

ከእዚህ በተጨማሪ የሃገራችን ሕዝብ ከፍተኛ ድጋፍ የሰጠው የቅንጅት ፓርቲ የሕዝብ ድምጽ እንዲከበር የወሰደው የጸና አቋም፣ ብሎም የሕዝብ ድምጽ ሊከበርባቸው የሚችልባቸውን የነጻ ተቋማት ምስረታው ጥያቄ ዋንኛው አድረጎ በመነሳቱ እና መሪዎቹም ይህ ጥያቄ ይመለስ በማለታቸው መስዋእትነት መክፈላቸው፣ የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄን በሕዝብ ዘንድ የበለጠ ክብደት እንዲሰጠው አድርጓል:: ለመጀመሪያ ግዜ የነጻ ተቋማት አስፈላጊነት ከፖለቲካ ልሂቁ ቋንቋነት ወደ ሕዝብ ቋንቋነት የተቀየረበት ሕዝብ እና የፖለቲካ ልሂቁ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የጋራ ጥረት ለማድረግ በጋራ የተሳሰሩበት ሁኔታን ፈጥሯል::

ዛሬ በሃገራችን በአንድ በኩል የሕዝብን ድምጽ አጭበርብሮ እና በጉልበት እረግጦ በስልጣን ላይ የተቆናጠጠው ዘረኛ እና አምባገነን መንግስት አለ:: በሌላ በኩል ድምጼ ተጭበርብሯል፣ ድምጼ ይከበር ሁለተኛም እንዲህ አይነቱ መጭበርበር እንዳይደገም መከላከል የሚችሉ ከፓርቲዎች ነጻ የሆኑ ተቋማት

ይፈጠሩ» የሚለው የመላው ሀፈሪቱ ሕዝብ አለ:: ቅንጅት ሕዝብን አማክሮ፣ ሕዝብም መብቱ እና ነጻነቱ መከበር በማይችልበት ዘረኛ እና አምባገናዊ የፖለቲካ ስርአት በተዘረጋበት ሃገር ምን ልትፈይዱ? እንዴትስ ብላችሁ ፓርላማ ትገባላችሁ በማለቱ ቅንጅት የነጻነት እና የመብት ዋስትና የሆኑት የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ በማንሳት ከሕዝቡ ጎን ቆሟል:: ለእነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች መሪዎቹ አባለቱ እና ደጋፊዎቹ በእንግልት በእስራት እና በሞት መስዋእትነት እየከፈሉ ነው:: ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሀገራችንን ሕዝብ በሙሉ፣ የፖለቲካ ልሂቃኑን ገበሬውን የከተማውን ነጋዴ እና የጉልት ተዳዳሪውን፣ ወንዱን እና ሴቱን ህጻናትን እና አረጋውያንን ክርስትያኑን እና እስላሙን በአንድ ላይ የአስተሳሰረ የፖለቲካ አጀንዳ የነጻ ተቀቋማት ምስረታ የፖለቲካ አጀንዳ ነው:: <u>**ይህ ግንቦት ያበረከተው የፖለቲካ እውቀት በሃገራችን ለተንሰራፉት የዘመኑ ዘረኛ አምባገነኖች ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የአምባገነንት ህልም ላላቸው ግለሰቦች እና የፖለቲካ ድርጅቶች የእግር እሳት እንደሚሆንባቸው በድፍረት መናገር ይቻላል:: ግንቦት 97 በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተሪክ ታለቅ የሚባለውን ድል ለሕዝብ አስረክቧል:: ከሕዝብ ዴሚክራሲያዊ ፈቃድ ወጭ ማንም የመንግስት ስልጣን ባለቤት መሆን እንደማይገባው ሕዝብ ግብቶታል:: ይህንን የአመለካት ብስለት ይዘን ብቻ ነው ከዚህ ወዴት የሚለውን ጥያቄ ማንሳት የሚገባን::**</u>

## *<u>5- ከተለወጠው ሁኔታ አንጻር ቅንጅት ወዴት?</u>*

ቅንጀት በግንቦቱ ምርጫ በመሳተፉ ታላቅ ድል አስመዘገበ:: ተስፋው እየመነመነ በራሱ እና በሃገሩ ላይ የነበረው አምነት እየሰለለ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአዲስ ስሜት እና መንፈስ አነሳሳው:: የወያኔን ዘረኛነት እና አምባገናዊነት እርቃኑን አስቀረው:: ሕዝብ በተለይ ደሃ ሕዝብ ከማናቸውም በላይ ለዴሞክረሲ ቀንአዊ እንደሆነ አሳየ:: ዴሞክራሲ የበለጸጉና በከፍተኛ ደረጃ የተማሩና የተመራመሩ ሕዝቦች ብቻ እሴት አለመሆኑን የኢትዮጵያ ደሃ እና ያለተማረ ሕዝብ ዴመክራሲያዊ መብቱን ለመጠቀም ባሳየው ትጋት እና ስነስርአት አረጋገጠ:: በሃገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአንድነት ያስተሳሰረ በከፍተኛ የፖለቲካ ተመክሮ እና እውቀት ላይ የቆመ ማንም ሊያስቆመው የማይችለውን የዴሞክራሲያዊ አንቅስቃሴ አስጀመረ:: ከሁሉ በላይ የሃገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ፣ የፖለቲካ ሰዎች በሙሉ፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መፈጠር የሚታገሉ ፖለቲካዊ ያልሆኑ የሲቪክ እና የሙያ መሃበራትን፣ ከእዚህም አልፎ በሃገሪቱ ዴሞክራሲ የለም በማለት ጠመንጃ በማንሳት የወያኔን አምባገነናዊ ስርአት እየታገልን ነው የሚሉትን ጦር የሰበቁ ድርጅቶች ሳይቀር፣ በአንድ ላይ ሊያስማማ፣ በአንድ ላይ ሊያሰባስብ የሚችል አንድ መሰረታዊ የፖለቲካ አጀንዳ ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ችሏል:: ይህ አጀንዳ ወያኔ የሕዝብን ድምጽ ዘርፎ፣ ለየፓርቲያቸው ሕዝብ የሰጠውን መቀመጫ ቀንሶ በጉልበት ባቆመው ፓርላማ ውስጥ ገብተው እጅ እና እግራቸው ተሳስሮ የተቀመጡትን ፓርቲዎች ጨምሮ ሁሉን ሊያስማማ የሚችል ነው::

አልፎ ተርፎም በእዚህ በአስራ አንደኛው ሰአትም ቢሆን ወያኔን እና ተለጣፊዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ እየጨለመ ያለውን መጪ የፖለቲካ እጣቸው ጀንበር እንዳይጠልቅ፣ በሰለጠነ መንገድ እራሳቸውን አስተካክለው የፖለቲካ ህልወናቸውን ማደስ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻ አጀንዳ ነው:: ይህ አጀንዳ ዛሬ፣ የቅንጅት መሪዎች፣ በሙቶ ሽዎች የሚቆጠሩ የደርጅቱ አባላት፣ደጋፊዎች እና የኢትዮያ ሕዘብ በአንድነት የቆሙሉት የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ነው::

ቅንጅት ያነሳው ጥያቄ ከድርጅቱ ብቸኛ ፍላጎቶች እና ጥቅም ጋር ብቻ የተሳሰረ አይደለም። «የሕዝብ ድምጽ ይከበር። ሕዝብ ለድርጅቱ የሰጠው ድምጽ ተጭበርብሯል» በሚል አቅጣጫ የተነሳ ጥያቄ ቢሆንም ጥያቄው ይህንን አልፎ ወደ ከፍተኛ እና መሰረታዊ ጥያቄነት ተሸጋግሯል። መሰረታዊ የሆኑ የነጻ ተቋማት ምስረታ ሳይኖር፣ የሕዝብ ድምጽ በስነስርአቱ ተቆጥሮ በሃገሪቱን ፓርላማ አብላጫ ወንበር ቢያዝ እንኳን፣ በየፓርላማው ተመራጭ ላይ መሳሪያ እየደገነ የሚተፋ፣ ተቆጣጣሪ የሌለው፣ በየቤቱ እየገባ የፓርላማ ተመራጮችን በጠራራ ጸሀይ የሚገድል፣ የደህንነት እና የጦር ሃይል በወያኔ እጅ እስካለ ድረስ በሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ በሕዝብ ድካምና ስቀይ ማሾፊያ፣ የአምባገነኖች መሳለቂያ ቀልድ ብቻ ሆኖ እንደሚቀር ግልጽ ሆኗል።

ዛሬ የፖለቲካ ጥያቄው የግንቦቱ ምርጫ ያስነሳቸውን የምርጫ እና የድምጽ ቆጠራ ውዝግቦች መፍታት መሆኑ ካበቃ ቆይቷል። ጥያቄው የግንቦቱ ምርጫ ያጋለጣቸውን የሀገሪቱን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ድክመቶች ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ መፍታት ሆኗል። ትግሉ መገናኛ ብዙሃኑ፣ ምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ ስርአቱ፣ ፖሊስ፣ ደህንነቱ እና ሰራዊቱ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ፍላጎት በመድፈቅ ከአንድ ፓርቲ ወግነው የተጫወቱት አፍራሽ ሚና እንዳይደገም ለማድረግ ነው። ሕዝብም ቅንጅትም በምርጫው የተጭበረበረ ድምጻችን ይከበር ከሚለው ጥያቄ ተሻግረዋል። ከእንግዲህ ወዲህ በአዲስ ምርጫ ወይም በተጨማሪ ማጣራት የሚመጣ ማንኛውም ተጨማሪ ወንበር የቅንጅቱ ሆነ የሕዝቡን የዴሞክራሲ ጥም የሚያረካው አይደለም።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር የሚለው ጥያቄ ነጻ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ እንደማይከበር ሕዝብም ቅንጅትም ያውቃሉ። ሌላ ምርጫ ይደረግ ቢባል ወያኔ ከተያያዘው በማጭበርበር እና በጉልበት ከመቀጠል አባዜው እንደማይቦዝን ያውቃሉ። ሕዝብ ከቅርቡ ልምዱ በመነሳት የመምረጥ እና የመመረጥ መብት እና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት የሚንከባከቡ ነጻ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ቅስቀሳ እና ጉትጎታ በገባበት ምርጫ የደረሰበትን ፍዳ ስለሚያውቅ ከአሁን በኋላ የወያኔን አፈጮሌዎች «የእንከን የለሽ ምረጫ» የሃሰት ፕሮፖጋንዳ አምኖ ዳግም በምርጫ እንደማይሳተፍ ግልጽ ነው።

የወያኔን ፍጹማዊ የሆነ አምባገነናዊ የስልጣን ሱስ በሚገባ ያልተረዱ ሰዎች እንደሚነግሩን፣ ወያኔ በሰውነታችን ማግኘት ከሚገባን መብት እና ነጻነት ቦጨቅ አድርጎ እንደውሻ የጣለልን በማያዝ፣ ጭራችንን ቀልፈን ፓርላማ ቅንጅት እንዲገባ ቢደረግ ከአምስት አመት በኋላ ተጠናክረን መምጣት ይችላል የሚል ቅዠት አላቸው። እነዚህ ሰዎች ሊረዱት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ከአምስት አመት በኋላ ግንቦቱ 97ቱ አይነት ምርጫ አይኖርም። ወያኔን የሚደግፉ የምእራብ መንግስታት ሳይቀሩ እየነገሩን ነው። የአፍሪቃ አምባገነኖች ምርጫን አስቀድመው ከምርጫ በፊት አጭበርብረው ነው በአሸናፊነት እውቅትና በመተማመን ወደ ምርጫ የሚገቡት። ወያኔ ድንቁርና እና እብሪት አጃጅለውት ምርጫ አሸንፋለሁ ብሎ መነሳቱ ግልጽ ነው። በሂደት እንደታየው ማሸነፍ አልቻለም። ከፍተኛ ውርደት ተከናንቦ በድምጽ ሌብነት ብቻ ሆኗል በስልጣን መቆየት የቻለው። «ወያኔ ከሚገባው በላይ ተኩራርቶ በከፈታት ምርጫ የደረሰበት ቅጣት አስከፊ በመሆኑ ሁለተኛ አይደገማትም እያሉን ነው» የምእራብ ሃገሮች ከፍተኛ ባለስልጣናት። ወያኔ ከስህተቱ ተምሯል። ሀእዚህ በኋላ መለስ ዜናዊ እንደ አፍሪቃ አምባገነን ወንድሞቹ ከምርጫ በፊት ሁሉን ጨርሶ ነው ይዋጣልን የሚለው።

ያለችንን ይዘን፣ ፓርላማ ገብተን፣ አዲስ አበባን ተረክበን፣ በሂደት ተጠናክረን እንወጣለን የሚለው ጉዳይ ጥቂቶችን ከወያኔ ቁጣ ነጻ ያወጣቸው ካልሆነ በቀር የኢትዮጵያን ሕዝቦች መከራ የሚያሳጥረው፣ የአዲስ አበባንም ሕዝብ ነጻነት እና ብልጽግና የሚያከናንበው አይሆንም:: ዴሞክራሲያዊ ስብእና የተከፈለ ባህርይ የለውም:: በሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች አፋኝ ስርአት ወያኔ ዘርግቶ በአዲስ አበባ ግን ቅንጅት የበላይነቱን ስላገኘ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ይፈቅዳል ብሎ ማውራት የአምባገነኖችን ምንነት በሚገባ ካለመረዳት የሚመነጭ አጓጉል ቀቢጸ-ተስፋ ነው:: አምባገነኖች ተጨንቀው እና ተገፍተው ካልሆነ በቀር በፈቃዳቸው የሚለቁት ስልጣን የለም:: በተለይ ባሁኑ ወቅት «የሃገሪቱን የዴሞክራሲ ሃይሎች እንዳሻችን ማድረግ እንችላለን፤ የትኛውም ምድራዊ እና ሰማያዊ ሃይል፣ የትኛዎቹም የሃገሪቱ ዜጎች እና የውጭ መንግስታት ጥረት ሊያድናቸው አይችልም» በሚል እብሪት የተቀበተተ መሪ በተንሰራፈበት ሁኔታ ያለታላቅ ተጋድሎ በአራዳነት ዴሞክራሲ መገንባት ይቻላል ማለት ትልቅ ስህተት ይሆናል::

ተቃዋሚዎች በየደረጃው ለወያኔ ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች እያነሱ፣ ሕዝብን ለማታገያ የወሰኗቸውን ውሳኔዎች እያጠፉ ተጉዘዋል:: ቅንጅት ይህንን ሲያደርግ ፍጥጫን በማስወገድ፣ ሰላምን መረጋጋትን በመጠበቅ፣ ሁሉም የሃገሪቱ ሕዝቦች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ አሸናፊ የሚሆኑበትን የዴሚክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት ለማስቀጠል በማሰብ ነበር:: ይህ አካሄድ ይሰራ የነበረው በስልጣን ላይ ያለው አምባገነን ድርጅት፣ አምባገነንነቱ ከድንቁርና የመጣ እንጂ በመሰረቱ ለሃገር እና ለወገን ቀና የሚያስብ ቢሆን ነበር:: ክፋት ከሌላቸው አምባገነኖችን (Benign dictators) ጋር ይህ አካሄድ ሊሰራ ይችል ይሆናል:: ወያኔ ግን የአክራሪ አምባገነኖች ( hard core) ጥርቅም ነው:: ስታሊን የሚባለውን የአምባገነኖች ጣኦት ሲያመልክ የመጣ ድርጅት ነው:: እምነቱ መግደል መዝረፍና መክዳት ነው:: መግቢያ መውጫው ካልጨነቀው ዘራፊነቱን ገዳይነቱን እና ጥላቻ አራማጅነቱን የሚያቆም አይደለም:: ይህንን የወያኔ ባህርይ አለመረዳት ብዙ ጉዳት አድርሷል:: አሁንም እንደገና ለወያኔ ተጨማሪ እጅ መንሻዎች እናቅርብና እናለሳልሰው የሚል ጥሪ የሚያቀርቡ ግብዣቸው በጉዳት ላይ ሌላ ጉዳት እንድንጨምር የማያደረግ መሆኑን ሁላችንም ልንረዳው ይገባል:: እንዲህ አይነቱ አመለካከት የወያኔን አምባገነናዊ ባህርይ ለመመከት የሚያስችል መስዋእትነት የሞላው ዝግጅት ከማድረግ ይልቅ ተዘናጊነትን ብሎም ተዋራጅነትን የሚጋብዝ ይሆናል:: እስካሁንም የታየው ይህ እውነታ ነው::

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና በሃገር ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ እንዲሁም ከሃገር ውጭ የሚገኘው የወገኑን የነጻነት እና የዴሞክራሲ ትግል ለመደገፍ ቆርጦ የተነሳው ኢትዮጵያዊ ሀገራዊ አርበኛ፣ የግንቦቱ ምርጫ በሕዝብ ፍላጎት እና ሕዝብ የሰጠውን ድምጽ ተከትሎ በሕዝብ አሸናፊነት ለምን እንዳልተጠናቀቀ ያውቃል:: የጦር ሃይሉ፣ ፖሊሱ፣ ደህንነቱ፣ ፍርድ ቤቱ፣ የምርጫ ቦርድ እና የሃገሪቱ መገናኛ ብዙሃን በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ባይሆኑ፣ እነዚህ ተቋማት ሕዝብ እና ሃገርን ህገ- መንግስታዊ በሆነ መንገድ ለማገልገል የተዋቀሩ ሆነው ቢሆን ኖሮ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹ ተከብሮ ከባርነት ከድህነት እና ከበሽታ የሚወጣበትን ጉዞ ከጀመረ አንድ መንፈቅ ይሞላው ነበር:: እነዚህ ተቋማት የአንድ ግለሰብ እና የአንድ ፓርቲ አገልጋዮች እንዲሆኑ ተደርገው በመቋቋማቸው ግንቦት በሆዱ ያዘለውን የሰላም የዴሞክራሲ እና የብልጽግና በረከት በናፍቆት ሲጠብቀው ለነበረው ሕዝብ ሳያድለው በኗል:: ይህ እወነታ ነው ሁላችንንም በነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ላይ ያስማማን፣ ሊያስማማን የሚችለው::

ከማናቸውም በሃገሪቱ ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በተሻለ በመዘርዘር፣ ቅንጅት በማኒፌስቶ ያቀረበውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የማህበራዊ ፖሊሲዎች ለጊዜው በእጥልጥል እንዲቀመጡ አድርጓል:: በእነዚህ ፖሊሲዎች ዙሪያም ለቅንጅት ድምጽ የሰጠው የቅንጅት ደጋፊ እነዚህ ፖሊሲዎች ሆኑ ወይም የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲ ፖሊሲዎች በስራ መዋል የሚችሉት ድርጅቶቹ በነጻ ተወዳድረው፣ ሕዝብ የሰጣቸውን እውነተኛ ድምጽ አስከብረው፣ ስልጣን ሲይዙ ብቻ እንደሆነ ያውቃል:: ይህ ደግሞ ያለ ነጻ ተቋማት ምስረታ የሚሳካ አይደለም:: ከፖለቲካ ጥያቄዎች ሁሉ የነጻ ተቋማትን ምስረታ ሕዝብ አግዝፎ እንዲያየው ያደረገው ይህ እውነታ ነው::

ዛሬ የነጻ ተቋማትን ምስረታ አስፈላጊነት ያልተረዳ፣ በነጻ ተቋማት ምስረታ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንደሚሆን ያላጤነ ግለሰብ፣ የፖለቲካ፣ የሙያ እና የሲቪል ድርጅት በሃገራችን የሚኖር አይመስለኝም:: ይህን ያልተረዳ ካለ አንድም ከወያኔ ጋር በጥቅም ከተሳሰሩ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ተለጣፊዎች መሃል መሆን አለበት:: አሊያም በራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም የማይተማመን፣ በሕዝብ ይሁንታ ሳይሆን በጠመንጃ ሃይል ወይም በማጭበርበር ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚፈልግ አምባገነን ወይም ጮሌ ብቻ ነው:: በችሎታው እና በሕዝብ ተቀባይነቱ የሚተማመን የነጻ ተቋማት ምስረታን ይደግፋል እንጂ አይቃወምም:: በራስ መተማመን ልቡን ሞልቶ በሕዝብ ፊት በመቆም ምረጡኝ በማለት ያሻውን የመንግስት ይሁን የሙያ እና የሰቪል ማህበራት መሪነትን መረከብ እንደሚችል ያውቃልና:: በፍትሃዊ ምርጫ ሕዝባዊ ተቀባይነትን እንደሚያገኝ በራሱ የሚተማመን ዴሞክራት በሃገራችን የተቀጣጠለውን የዴማክራሲያዊ ተቋማት ትግል ከመደገፍ የተሻለ ሌላ የትግል እና የማታገያ አጀንዳ ማንሳት የሚችል አይመስለንም::

በሃገራችን ዴሞክራሲን አፍኖ፣ የህግ የበላይነትን ረግጦ በማን አለብኝነት የሀገር እና የሕዝብ ሃብት እየዘረፈ፣ ዘረኛ እና አምባገነናዊ የሆነውን ስርአት ለማስቀጠል በሚጥረው በወያኔ ላይ የተነሳው ተቃውሞ በየቀኑ እያደገ ነው:: ይሁንና በተደራጀ መልኩ በሕዝብ ስም ይህንን ትግል የሚያኪያሂዱት ሃይሎች፣ ከደካማው አስከጠንካራው፣ በሰላማዊ መንገድ ከሚታገለው ወይም ሰላማዊ መንገዱን ወያኔ ስለዘጋበት በምሬት ዱር ቤቱን ያደረገው ጦረኛ ሳይቀር፣ ማወቅ ያለባቸው ከአሁን በኋላ በሃገራችን የሚያዝ ስልጣን በቅድሚያ በሰላም፣ በህገመንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ እና በሕዝብ ይሁንታን ላይ የሚመሰረት ብቻ እንደሆነ ነው::

ሕዝብ የስልጣን ምንጭነቱን አውቋል:: ገዥዎች ለዘመናት ጭነውበት የነበረውን ፍራቻ ሰብሮ ዳግም ወደ ባርነት እንደማይመለስ ግልጽ አድረጓል:: ከዛም አልፎ የነጻነት እና የዴሞክራሲ መብቶቹ በግለሰቦች በጎ ፈቃድ የሚሰጡ ወይም የሚከለከሉ ሳይሆኑ፣ በተፈጥሮው፣ በሰውነቱ እና በዜግነቱ የተላበሳቸው የማይገፈፉ መብቶቹ እንደሆኑ አጥርቶ ተረድቷል:: ከእዚህም በተጨማሪ መብቱ የሚከበረው በግለሰቦች ወይም በቡድኖች በጎ አድራጊነት ሳይሆን ሁሉንም ዜጋ በእኩልነት ለማገልገል በተቋቋሙ የዴሞክራሲ ተቋማት አማካይነት ብቻ እንደሆነ ከግንቦቱ ተመክሮው የማይረሳ ትምህርት ቀስሟል:: ከአሁን በኋለ በጉልበት ወይም በነጻ አውጭነት ምህላ መጥቶ ስልጣን ላይ ማንም የሚፈናጠጥበት እድል አይኖረውም:: ይህ ሀገራዊ እውነታ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ በእኩልነት፣ በሕዝብ ፊት እኩል ሃሳባቸውን የመግለጽ፣

ሕዝብን የማደራጀት፣ ሕዝብን ድምጽህን ስጠን ይሁንታህን ለግሰን በማለት በሕዝብ ምርጫ ስልጣን ከሚይዙበትን ሁኔታ ውጭ ሌላ ወደ ስልጣን መውጫ አቋራጭ መኖር እንደማይኖር ሕዝብ ገብቶታል፡፡

በሰላም ይሁን በጠመንጃ ሃይል የሚታገለው በሙሉ የሕዝብን ይሁንታ ሳያገኝ፣ ሕዝብ የተለያዩ አማራጮች በነጻ ቀርበውለት እና በነጻ መምረጥ ሳይችል ለሕዝብ የሚበጀውን የማውቅለት እኔ ብቻ ነኝ በሚል እብሪት ተነሳስቶ ስልጣን መውጣት የሚቻልበት ዘመን ማለፉን ሁሉም ቢገነዘበው የተሻለ ይመስለናል፡፡ ከእዚህ ውጭ የሚያስበ ካሉ የመንግስቱ ሃይለማሪያም እና የመለስ ዜናዊ አይነቶቹን አምባገነናዊ ስርአቶች ለማቆም ያኮበከቡ ጫጩት ፋሽስቶች ብቻ ናቸው፡፡ ለእዚህ ነው ዛሬ ቅንጅት ያነሳውን እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች መስዋእትነት እየከፈሉለት ያለውን የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ የትኛውም በዴሞክራሲ የሚያምን የፖለቲካ ድርጅት ሊደግፈው እና ሊታገልለት ይገባል የምንለው፡፡ የሚታገለው ለቅንጅት ሳይሆን ለራሱ ዴሞክራሲያዊ ህልውናና እወደዋለሁ ለሚለው ሕዝብ እና ሃገር ሲል ብቻ ነው፡፡

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ፣ የተለያዩ የፖለቲካ አላማ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ድረጀት፣ የተለያዩ የሲቪክ እና የሙያ ማህበራት እንደ ማህበራት በነጻነት ህልውናቸው ተጠበቆ መቀጠል የሚችሉበትን ዋስትና የሚሰጠውን የነጻ ተቋዋማት ምስረታ ትግል በዋንኛ ነት የተሸከመው የፖለቲካ ድርጅት ሆኗል፡፡ ይህ የዴሞክራሲ ተቋማት ምስረታ ትግል በሚሊዮን በሚቆጠሩ የሀገሪቱ ሕዝቦች የተደገፈ ነው፡፡ ቅንጅት እና መሪዎቹ አበሳቸውን እያዩያሉት ያለው የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ጠባብ የድርጅት ጥቅም ለማስከበር የተሰነዘረ አይደለም፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ከደገፉት የፓርቲውን የፖለቲካ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ፖሊሲ ሕዝብ ሃገር የፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ፖሊሲዎች ተሻግሮ፣ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የቅንጅትን ፕሮገራም ተጻረው በሕዝብ ፊት በነጻ ተወዳድረው እራሱን ቅንጅትን ሳይቀር ማሸነፍ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው፡፡

ዛሬ ቅንጅት ከበሀገር ውስጥ እና ከሃገር ውጭ በማግኘት ላይ ያለውን ከፍተኛ ተቀባይነት እና ድጋፍ ከእዚህ በፊት በሃገራችን እንደታዩት ያውም የቅንጅትን ያህል ድጋፍ ያልነበራቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳደረጉት ስልጣንን ለብቻው በሞኖፖል ለመያዝ ለሚደረግ ትግል የመጠቀም ፍላጎት የለውም፡፡ የተራ ፍላጎት ማጣት ብቻ ሳይሆን በእዚህ መንገድ ስልጣንን በሞኖፖል መያዝ ትክክል ነው ብሎ ስለማያምን ነው፡፡ ይህ አማራጭ በሕዝብ ውሳኔ ሳይሆን በአንድ ድርጅት ውሳኔ ብቻ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከፖለቲካው መንገድ ኢዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲወገዱ የሚያደርግ በመሆኑ መልሶ ሃገራችንን እና ሕዝቦቿን ለሌላ ዙር ሁካታ የሚያመቻች ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነቱ የስልጣን ስግብግብነት ሕዝብን በነጻነት፣ በሰላም እና በብልጽግና ሰቀቀን እንዲያለቅ ያደረገው ያው ያረጀ እና ያፈጀ የአምባገነኖች መንገድ እንደሆነ ቅንጅት ያውቃል፡፡

ቅንጅት የሃገሪቱ ሁለንተናዊ ችግሮች በሙሉ ሊፈቱ የሚችሉበትን ቁልፍ ጥያቄ አንስቷል፡፡ የእዚህን ጥያቄ ሀገራዊ እርባና፣ የድርጅቱ አመራር ብቻ ሳይሆን፣ አመራሩን የዴሞክራሲ መብቶች በሌለበት ሃገር፣ የሕዝብ ድምጽ ተዘርፎ በተቋቋመ አሻንጉሊት ፓርላማ አትግቡ ብሎ ጥብቅ መመሪያ የሰጠውም ሕዝብ

ተገንዝቦታል። አመራሩ ብቻ ሳይሆን ለአመራሩ መብቴን አስከብሩልኝ በማለት የተማጸናቸው ሕዝብ ለነጻ ተቋማት ምስረታ ከፍተኛ መስዋእትነት እየከፈለ ነው። አሁን ባለንበት ወቅት በእዚህ መሰረታዊነቱ ለዘመናት በሚዘልቀው ቁልፍ የፖለቲካ ጥያቄ ዙሪያ የተቀጣጠለውን ትግል አጠናክሮ ከመቀጠል ሌላ ቅንጅት ምንም ሌላ አማራጭ የለውም። ማንኛውም ውይይት፣ ድርድር፣ ስምምነት፣ ህብረት እና መደጋገፍ በእነዚህ ሁሉንም የሀገሪቱን የፖለቲካ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ህይወት ቁልፎ ከያዘው የነጻ ተቋማት ምስረታ ጋር ብቻ በመያያዝ የሚደረግ ነው።

የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ለቅንጅት ሕዝብን ማታገያ የጊዚያዊ ታክቲክ ጥያቄ ብቻ አይደለም። የሕዝብ ድምጽ ባለመከበሩ ወቅታዊ ከሆነ የፖለቲካ ቀውስ ጋር በመያያዘ የተነሳ ቢሆንም መሰረታዊ የስትራተጂ ጥያቄ ነው። ለመጀመሪያ ግዜ በታሪካችን የፖለቲካ ስልት እና ግብ፣ ጊዚያዊ የመታገያ መፈክር እና የስትራተጂ ጥያቄ አንድ የሆኑበትን ሁኔታ አስከትሏል። ይህ የሚያሳየው ስልጣን መያዝ ብቻ ሳይሆን ስልጣን የሚያዝበት ስልት በራሱ ትረጉም ያለው ጉዳይ መሆኑን የተረዳ የፖለቲካ ባህል እድገት ባሀገራችን መከሰቱን የሚጠቁም ነው።« የትም ፍጪው ስልጣኑን አምጪው» በሚል ጭፍን የስልጣን ጥማት የሚነዳ የፖለቲካ ባህል ካስከተለው ጥፋት ህብረተሰባችን ትምህርት መውሰዱን የሚያረጋግጥ ነው። ቅንጅት፣ ይህንን እድገት ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በሚያስችል የትግል አቅጣጫ መሄድ ብቻ ነው ያለው አማራጭ። ከእዚህ ጥያቄ የተሟላ መልስ ማገኘት ውጭ ሌላ ምርጫ የለውም። የሀገራችን ሕዝብ ያሳየው ቁርጠኛነት እስከአሁን የከፈለው መስዋእትነት ከነፃ ተቋማት ምስረታ በታች የሚወርድ ድል አይመጥነውም። እንዲህ አይነቱ ትግል ለማስቀጠል የሚያስቸል ከፍተኛ ምሁራዊ ብቃት እና የራእይ ጥራት ያለው አመራር አለው።

በተመሳሳይም ይህንን ራእይ የሚጋራ ተመሳሳይ ምሁራዊ ብቃት ያለው ከፍተኛ የምሁር ክምችት በደጀንነት የቆመለት ድርጅት ነው። ከሁሉም በላይ ለመጀመሪያ ግዜ ህዝብ እና የሃገሪቱ ሊቃውንት በአንድ ላይ የተሳሰሩበት የፖቲካ ጥያቄ በመሆኑ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ጥያቄው መልስ ማግኘቱ አይቀርም። ቅንጅት፣ የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ እና የወያኔ ምላሽ የወያኔ ዘረኛ እና አምባገነናዊ የፖለቲካ ስርአት ዴሚክራሲ ባለበት እና የነጻ ተቋማት በተመሰረቱበት ሃገር እንኳን አስራ አምስት አመት አንድ ሳምንትም እድሜ እንደማይኖረው ይታወቃል።

ወያኔ አሸንፋለሁ በማለት ያዘጋጀው የምርጫ ድራማ በተሸናፊነት እንደሚጠቃለል በተረዳበት ወቅት ወደ ማጭበርበር ወደ እስራት እና ግድያ ሄደ። የጦር ሃይሉን፣ ስላለውን፣ ፖሊሱን ፍርድቤቱን እና የመገኛኘ ብዙሃኑን እንዳሻው ማዘዝ የማይችልበት ሁኔታ በሀገሪቱ ቢፈጠር ወያኔ በውድድር ስልጣን መያዝ ቀርቶ እንደ ፖለቲካ ድርጀት መቀጠል የማይችል እንደሆነ በምርጫው ወቅት ሕዝብ ካሳየው ግልጽ እና የመረረ ተቃውሞ ተገንዝቦታል። ወያኔ ተዘርዝሮ የማያልቅ፣ ከሃገር ክህደት ጋር፣ ከዘር ማጥፋት ጋር፣ በሃገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የሕዝብ እና የሀገር ሃብት ዘረፋ ጋር የተሳሰሩ በርክታ እና ግዙፍ ወንጀሎችን ሲፈጽም የኖረ መሆኑን ያውቃል። ለእነዚህ ወንጀሎቹ አስካሁን ያልተጠየቀው በሃገሪቱ ነጻ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት እንዳይኖሩ ለማድረግ በመቻሉ እንደሆነ ይታወቃል። የወያኔ ወንጀል ግዙፍ እና በርካታ ከመሆኑ የተነሳ «ሽህ ግዜ ግድ የለህም ሀገሪቱ እና ሕዝቧ ለጠማቸው ሰላም፣ ለሚፈልጉት ዴሞክራሲና ብልጽግና ስንል አንጠይቅህም ተብሎ ምህላ ቢገባለትም ማንንም አያምንም። የፈጸማቸውን ወንጀሎች ይቅር የሚል

ደግ እና ቸር ህሊና በእዚህ ምድር ይኖራል ብሎ አያምንም። በመሆኑም ዛሬ ወያኔ ይህንን ቃል የገባለትን አርቆ አሳቢ የቅንጅት ድርጅት ከማናቸውም ድርጅቶች በላይ ለይቶ፣ መሪዎቹን፣ አባላቱን እና ደጋፊዎቹን በገፍ በማሰር እና በመግደል በሃገራችን ሌላ ቀይ ሽብር እያኬሄደ ነው። የነጻ ተቋማት ምስረታው ትግል በዋንኛነት የሚመራው በቅንጅት መሆኑ ነው የወያኔ ግፍ እና በደል በቅንጅት አባለት ላይ የተጠናከረው። ከእዚህ ውጭ ቅንጅት እና መሪዎቹን በሚመለከት ነጋ ጠባ፣ በሞኖፖል በያዘው ሬድዮን እና ቴሌቪዥን የሚያናፋው ተራ ማጭበርበር ነው። የቅንጅት አመራር የጀመረው እንቅስቃሴ የወያኔ ስልጣን የቆመበትን ፍትሃዊ ያለሆነ መሰረት የማይጋፋ፣ ወያኔ በማንኛውም መመዘኛ ሊይዘው ከማይገባው ስልጣን የማያወርደው ትርጉም አልባ እንቅስቃሴ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ የሃሰት ክስ በቅንጅት መሪዎች ላይ አይመሰርተባቸው ነበር። ከጠዋት አስከማታም ዘራቸው፣ የፖለቲካ ታሪካቸው እና ህይወታቸው ላይ በቆርጦ ቀጥል ፕሮፓጋንዳ ላይ የተመሰረተ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ስራ የሚካሄድበት ምክንያት አይኖርም ነበር።

ወያኔ ዛሬ የሚያስጨንቀው በፓርላማ ውስጥ ገብተው ፋይዳ የሌለው ተቃውሞ የሚያሰሙ የፖለቲካ ድርጅቶች አይደሉም። እነዚህ የፈለጉትን ሃይለ ቃል እየተጠቀሙ እና የፈለጉትን ነገር መናገር የሚችሉበትን ሁኔታ ወያኔ በፍቃዱ ሊፈጥርላቸው ዝግጁ ነው። በፓርላማው ውስጥ ያለውን ሃሳብ የመግለጽ ነጻነት ለአለም ለማሳየት የሞቀ ክርክር በፓርላማ ውስጥ እንዲደረግም ወያኔ ትእዛዝ መስጠት ይችላል። እንዲህ አይነቱ ትርጉም የለሽ ጩህት ባለፉት ሁለት ፓርላማዎች የታየ ነው። ፓርላማ ያለ ነጻ ተቋማት ምስረታ ትርጉም የለውም። ነጻ ተቋማት ባሉበት ሀገር ግን የፓርላማ አብላጫ ወንበር አንድ የፖለቲካ ድርጅት ሳይዝም ብዙ ቁም ነገሮች ለሀገር እና ለወገን መስራት ይችላል። ሁለም ለሃገር እና ለወገን የሚያስብ ቢሆን ፓርላማ ተገብቶም ቢሆን ሳይገባ በሚደረግ ድርድር እና ምክክር የነጻ ተቋማትን ምስረታ ማከናወን ይቻል ነበር። ነገር ግን ዛሬ በወያኔ እጅ የሚገኘው ፓርላማ ውስጥ መገኘት የወያኔን ሀገራዊ ክህደት እና የዘረኛነት እና የዘረፋ ስርአቱን ማስቆም ቀርቶ፣ እየተጠናከረ የሚሄድበትን ፍጥነት መቀነስ የሚያስችል አቅም ለተቃዋሚዎች የሚሰጥ አይደለም። ፓርላማውን ከሕዝብ በተዘረፈ ድምጽ አብላጫውን ወንበር የያዘ መንግስት፣ ከፍተኛና የአፈና መዋቀር በቁጥጥሩ ስር ያለው መንግስት፣ ሲፈልግ በፓርላማው ያለውን አብላጫ ድምጽ የህግ ከላላ በማድረግ የፈለገውን ህግ ለማውጣት እንደሚችል በተግባር ያሳየ መንግስት፣ በእዚህ መንገድ መሄዱ ደግሞ ደስ ካላለው ከፓርላማ ውጭ የሚያዘቸውን የአፈና መዋቅሮች በማነቃነቅ ያሻውን ከመፈጸም የሚያግደው ምንም ነገር እንደማይኖር ያውቃል። ወያኔ በሁሉም ነገሮች ላይ ለመነጋገር ፈቃደኛ ነኝ ነገር ግን የነጻ ተቋማት ምስረታ ጉዳይ አታንሱብኝ የሚለው ለእዚህ ነው።

ወያኔ በቅንጅት ላይ እየወሰደ ያለው የጥቃት እርምጃ መሪዎቹን እና አባላቱን ከማሰር እና ከመግደል አልፎ ድርጅቱን እንደ ድርጀት ለማጥፋት የታለመ ነው። የተለመዱትን ከወያኔ ቁጥጥር ውጭ ህልውና የሌላቸውን የምርጫ ቦርድ እና ፍርድ ቤቶች በመጠቀም፣ ቅንጅት የሚባል ነገር የለም ማለት ጀምሯል። በሌላ በኩልም ማለቂያ በሌለው የተዘረፈ የሕዝብ ሃብት የሚደልላቸውን የቅንጅት ተመራጮች በመጠቀም ቅንጅት የሚባል ሌላ ተለጣፊ ድርጅት ለማቆም እየተራወጠ ነው። በአሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስ ላይ የተሰራውን አይነት ተለጣፊ የመፍጠር ድራማ በቅንጅት ላይ ለመድገም እየተሞከረ ነው። በሌላ በኩልም በቅንጅት ስም ተወዳድርው ሕዝብ በእዚሁ ምክንያት ብቻ እድል የሰጣቸው ሕዝብ የካዱ የወያኔ

ቅጥረኞችን በመጠቀም ከቅንጅት ውጭ በሌላ ድርጅት ስም እንዲንቀሳቀሱ አድርጓል:: ሌሎችም የቅንጅት ተመራጮች ከቅንጅት ውጭ የራሳቸውን ሌላ ድርጅት አቁመው እንዲንቀሳቀሱ ወያኔ ማለቂያ የሌላቸውን ሴራዎቹን እየሸረበ ነው:: በሁኔታው ተገደው ፓርላማ ቢገቡም የሚደርስባቸውን ተጽእኖ በመቋቋም ሕዝብ በቅንጅትነታቸው የመረጣቸውን የፓርላማ አባለት በጋራ እንዳይንቀሳቀሱ መንገዱ ሁሉ እንዲዘጋባቸው ተደርጓል::

በሌላ በኩል ሕዝብ እውነተኛ ስሜቱን መግለጽ የሚችልባቸው የሰላማዊ ሰልፍ እና ስብሰባ ማድረግ ዴሞክራሲያዊ መብቶች አፍነዋል:: በምርጫ ድምጹን የሰጣቸው የቅንጅት ተመራጮች ድምጹን በቅንጅትነት ከወሰዱ በኋላ ለሌላ ድርጅት መጠቀሚያነት ሲያወሉት በህገ-መንግስቱ መሰረት አይወክሉኝም በማለት ከፓርላማ ማስወጣት የሚችል እንቅስቃሴ መጀመር እንዳይችል በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ መብቱን በማፈን ወያኔ ለከሃዲ ግብረአበሮቹ ከላላ እየሰጠ ይገኛል:: የመለስ ዜናዊን ሃገራዊ ክህደት በመቃወማቸው ከወያኔ ድርጅት አባልነታቸውን በጸጥታ ሃይሎች የተገፈፉት ከፍተኛ የወያኔ አመራር አካላት ከፓርላማ ጭምር እንዲወገዱ ወያኔ ያደረገውን እናስታውሳለን:: በህገ-መንግስቱ ውስጥ የተቀመጠውን፣ መራጮች ተወካዮቻቸውን ከፓርላማ የማንሳት መብታቸውን በመጠቀም የሕዝብ የይነሱልን ፊረማ በማሰባሰብ ነበር:: ወያኔ ይህንን ፊርማ ያሰባሰበው በማስፈራራት እንደነበር ይታወቃል:: ይሁንና ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በስሙ የሚነግዱትን የፓርላማ አባላት አይወክሉኝም በማለት ተመሳሳይ ፊርማ ማሰባሰብ ከፓርላማ ማባረር አይችልም:: ህዝብ ይህን የማድረግ ህገ-መንግስታዊ መብቱ በወያኔ አሸባሪነት ታፍኗል:: ይህ መብት ለሕዝብ ተከብሮ ቢሆን ዛሬ ሕዝብን ክደው ለወያኔ ማገልገል ከጀመሩት ተመራጮች መሃል አንዳቸውም ፓርላማ ውስጥ ተቀምጠው ወፍራም ደሞዛቸውን እየዋጡ መቀጥል አይችሉም ነበር::

በሃገሪቱ ውስጥ ወያኔን የሚቃወሙ፣ በዘረኛነት ምትክ አንድነትን፣ ከሃገራዊ ክህደት ይልቅ ሃገራዊ ክብር፣ ከሃይማኖት እና የዘር ግጭት ከማራገብ ይልቅ መቻቻልን፣ ከዘረኛ አድሎ ይልቅ ሁሉንም ዜጋ በእኩልነት ማስተናገድን፣ ከሕዝብ ሃብት ዘረፋ ይልቅ ሃቀኛነትን፣ ከድንቁርና ይልቅ እውቀትን፣ ሆድ ለሞሙላት ሲሉ ከመነዳት ይልቅ ለሰብአዊ ክብርን አስቀድሞ መቆምን የመረጡ ግለሰቦች እና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳይኖሩ ማድረግ ነው:: ወያኔ እነማን መርጦ እያሳደደ ነው? እነማንን አሰረ? አነማንን እየመረጠ እያገለለ ነው? ከነማን ጋር ነው እየተቀራረበ ያለው? ከእነማን ጋር ነው በአንድ ማዕድ እየቆረሰ ያለው? ከተለጣፊዎች ጋር ነው ወይም ከሕዝብ እውነተኛ ተወካዮች ጋር:: የራሳቸው ክብር ካላቸው ሰዎች ጋር ወይስ ተራ ህብረተሰባዊ ይሉኝታ እንኳን ከማያይገዛቸው ከሃዲዎች ጋር? እውቀት ካላቸው ወይስ ድንቁርናውን በአዋቂነት ሊያጋንኑለት ከሚችሉ ከእርሱ የባሱ ደናቁርት ጋር? የታሰሩትን፣ የተገለሉትን እና በፓርላመው ውስጥ ሆነ ከፓርላማው ውጭ ወያኔ በአይነ ቁራኛ የሚያያቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች እና የድርጅቶቹ መሪዎችን ዝርዝር በማየት በቀጥታ መልሱን ማግኘት ይቻላል::

ወያኔ በቅንጅት መሪዎች እና በሌሎችም ፖለቲካ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች አባላት እና ደጋፊዎች ላይ ከግንቦቱ ምርጫ ጀምሮ በመውሰድ ላይ ያለው እርምጃ የሚያሳየው አንድ ነገር ብቻ ነው:: በምንም አይነት በሕዝብ ተቀባይነት ያላቸው በሕዝብ የሚደገፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማየት አይፈልግም:: ስላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የወያኔን ፈቃድ የሚያገኘው የወያኔን ስልጣን እስካልተጋፋ ድረስ ብቻ ነው:: ወያኔ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚፈልጋቸው አምባገነናዊ አገዛዙ እርቃኑን እንዳይቀር እና

በዴሞክራሲያዊነት ስም ከምእራብ መንግስታት የሚያሰባስበው የአባለቱ የተቀናጣ ኑሮ መሰረት የሆነውን የንዘብ ምንጭ እንዳይደርቅበት ብቻ ነው። ከእዚህ ውጭ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በራሳቸው መቆም ያለባቸው፣ ለሕዝብ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን አቅርበው በመመረጥ ስልጣን ላይ የመውጣት አላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ፣ ይህም መብታቸው እንደሆነ ወያኔ አያምንም። ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሕይወት ማለት ስልጣን ላይ መውጣት እና ከስልጣን መውረድን እንደሚያጠቃልል ወያኔ አይቀበልም። በግንቦቱ ምርጫ የተደረገው አይን ያወጣ ማጭበርበር፣ ከእዚያም በኋላ ለቀረበለት የብሄራዊ አንድነት መንግስት ጥያቄና በኋለም ስለነጻ ተቋማት ምስረታ ከቅንጅት የቀረበለትን ሰላማዊ እና ህጋዊ ጥያቄ ወያኔ አላዳምጥም ያለውም ለእዚህ ነው። ከእንዲህ አይነቱ ድርጅት የፖለቲካ ስልጣኑን በተቆጣጠረበት ሁኔታ በህጋዊነት እና በሰለማዊ መንገዶች የሚደረገው ትግል ከመርፌ ቀዳዳ የጠበበ እየሆነ መጥቷል።

በተጭበረበረ ፓርላማ ውስጥ ገብተው፣ የወያኔን አምባገናዊነት ተቀብለው፣ ምንም አይነት እርባና ያለው ስራ ሳይሰሩ በየወሩ የሚሠጥን ከፍተኛ ደሞዝ እየበሉ ለመኖር የወሰኑ« የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች» አመራር እና አባለት መኖራቸው፣ ሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻልበት እድል እንዳለ አድርጎ ለመከራከር የሚዳዳው ከአለ ለቅጥረኛ ብቻ ነው የሚሆነው። ከእንዲህ አይነቱ ቅጥረኛ በስተቀር በፓርላማ ውስጥ ተገደው ወይም ከግል ጥቅም ጋር ባልተሳሰረ መንገድ የገቡት የሕዝብ አደራ እና ሃገራዊ ተቆረቋሪነት የሚሰማቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች የማይክዱት ሃቅ ቢኖር ወያኔ የፓርላማ አሻንጉሊት ያደረጋቸው መሆኑን ነው። ማናቸውም በእዚህ ፓርላማ ውስጥ የሚገኙት ሃይሎች በሙሉ ዛሬ ወያኔ ህግን በመጣስ በሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን እመቃ ለመቃወም ህገ-መንግስቱ የሚፈቅደውን የሰላማዊ ሰልፍ፣ የስራ ማቆም አድማ እና ሌሎችን የትግል ስልቶች እንጠቀማለን ቢሉ፣ መዘዙ ምን ያህል አስከፊ እንደሚሆን ያውቃሉ። የፓርላማ አባል በመሆን ተመራጮች አላቸው የሚባለው ህገ-መንግስ5ዊ የህግ ከላላ ሳያግደው ወያኔ ሊያስራቸው እና ሲያሻው ሊገድላቸው እንደሚችል የሚዘነጉት አይመስለንም። ያለነጻ ተቋማት በወያኔ ፓርላማ በመግባት ለዴሞክራሲን መጎልበት ትግል ማድረግ ይቻላል የሚሉንን እባካችሁ ስለፈጣሪ ብላችሁ ተውን ከማለት ሌላ ብዙም ማለት የሚቻል አይመስለንም። «ለነፍሴ ለንብረቴ ፈራሁ፣ ለሚሰጠኝ ከፍተኛ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ተረታሁ፣ በፓርላማ ውስጥ ከረቫቴን አንዝርጌ በመቀመጥ የሚሰማኝ ኩራት በለጠብኝ» ብሎ መናገር ይሻላል።

ህጋዊ እና ሰላማዊ ናችሁ ብለው፣ በወያኔ የተቋቋሙት፣ የምርጫ ቦርድና ፍርድ ቤት ፈቃድ የሰጧቸው ድርጅቶች በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ ይፈርሳሉ። የፖለቲካ ድርጅቶች ህጋዊነት አግኝተው የከፈቷቸው ቢሮች ይወረራሉ። ንብረቶቻቸቸው ይወረሳል። መንግስት በህጋዊነት እንዲንቀሳቀሱ መብት የሰጣቸው፣ ቢሮ ሲከፍቱ ዝም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አባል መሆን በወንጀል ያስጠይቃል።፣ ሕዝብ ስሙን፣ አድራሻውን፣ ለድርጅቱቹ የሰጠውን ገንዘብ እና ሌሎች ህጋዊ ድጋፎች የተመዘገበበትን ዶሴ የድረጅቶቹን ቢሮ ህገወጥ በሆነ መንገድ በወያኔ ሴኩሪቲዎች እየሰበሩ በመውሰድ አባላትን ከየቤታቸው እየለቀሙ ማሰሪያ፣ ደስ ካላቸውም መግደያ አድርገው ይገለገሉበታል። አባላት ህጋዊ በሆነ ድርጅቶች ውስጥ በመሳተፋቸው ከስራ ይባረራሉ። የንግድ ፈቃቸው ይሰረዛል። ከቦታ ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ ይደረጋል። ከህግ ውጭ ቤታቸው ይበረበራል። ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብለው ያስቀመጡትን ጥሪት በጠራራ ፀሐይ ይዘርፋሉ። ይህ ብዙ ያልተነገረው የወያኔ ወታደሮች በየቤቱ እየገቡ የዘረፉት ገንዘብ እና ወርቅ እንዲሁም ውድ

ቁሳቁሶች በሚሊዮኖች ብር የሚገመት ሆኗል። ዜጎች ከጠዋት እስከማታ በደህንነት አባላት ክትትል ይደረግባቸወል። ሰብአዊ ክብራቸውን የማኒካ ግፍ ይፈጸምባቸዋል።

ወያኔ እራሱ በክርክር ግጠሙኝ በማለት በፈቀደው የክርክር መድረክ የተሰጡ ነጻ አስተያየቶችን ለክስ ማስረጃ ሆነው እየቀረቡ ነው። በወያኔ ህገመንግስት የተቀመጡ የሰላማዊ ተቃወሞ መብቶቹን ለመጠቀም ጥሪ ያደረጉ ድርጅቶች እና መሪዎች ህገ- መንግስቱን ለመናድ የሚል ክስ ይመሰረትባቸዋል። ወያኔ እራሱ ገድሎ «እዩዋቸው እንድገድል አደረጉኝ» ብሎ የሚቾችን ወገኖች ያስራል። እንደ ደርግም የሚቾችን እሬሳ እየሸጠ በሕዝብ ደም የተጨማለቀ እጁ ሳይደርቅ በየሽራተኑ በውድ ከኛክ የተሞላ ብርጭቆውን ህጻናት ሲገሉ ከዋሉ አግአዚዎቹ እና አጨብጫቢወቹ ጋር ለጤንነቱ ያጋጫል። «ሁሉም ነገር ይቅርብኝ እጅ እና እግሬን ሰብስቤ እቤቴ እቀመጣለሁ» ያለውን «ለምን እቤትህ ትቀመጣለህ?» በማለት፣ ሰው በገዛ ህይወቱ እና በገዛ ንብረቱ ላይ ማዘዝ የሚችልበትን ፍጹማዊ የሆነ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት በመጣስ በግድ ከቤትህ ውጣ፣ በግድ ሱቅህን ክፈት የሚል የድንጋይ ዘመን አስተሳሰብ እና አገዛዝ፣ የድንጋይ ዘመን ባልተሸገሩ ገዝዎቹ ሕዝብ ተጭኖበታል።

እንዲህ አይነቱ ማናቸውም የህግ ከላላ የሚባል ነገር በሌለበት ሃገር፣ ወያኔ በዜጎች ህይወት እና ንብረት ላይ እንዳሻው በሚያዝበት ሃገር፣ እንዴትስ ነው ሕዝብ መብቱን ለማስከበር ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሰው። እንዴትስ ነው የመንግስት ተቋማት ባለስልጣናት እና ተቋማቱ አንጻራዊ ነጻነት በሚሰማቸው ጆርጅያ እና ዩክሬንን በመሳሰሉ ሃገሮች የተደረገው ሰላማዊ የዴሞክራሲ የትግል ስልት ወያኔን የመሰለ አረመኔ እና ኋላ ቀር መንግስት ባለበት የሃገራችን ሁኔታ መካሄድ የሚችለው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በኢትየጵያ፣ የሚሊተሪ እና የሲቪል ቢሮክራሲውን የሚያዙት የመንግስት በላስልጣናት እንስሳዊ በሆነ መንገድ በሆዳምነታቸው፣ ከዘረኛዎቹ የወያኔ ገዥዎች ጋር ተሳስረዋል። ይህ ሃቅ በህሊናቸው የሚመሩ ስልጡን የሆኑ የጦር፣ የፖሊስ አዛዦች እና የፍርድ ቤት ዳኞች ባሉባቸው ዩክሬንን እና ጆርጂያን በመሰሉ ሃገሮች የተካሄደውን የሰላማዊ ትግል ስልት ለመኮረጅ በምናደርገው ጥረት ፊት ደንቃራ አይሆንብንም ወይ? እውን ይህ የጆርጂያን እና የዩክሬንን ሕዝቦች የትግል ስልት ኩረጃ ከእዚህ ቀደም የሃገራችንን ነባራዊ እወውነታ ግምት ውስጥ ሳናስገባ ካደረግናቸው አጥፊ ኩረጃዎች መለየት የምንችለው? እንደ ጋንዲ በሰላም ስንል፣ የጋንዲን ሰላማዊ እንቅስቃሴ የፈቀደው የእንግሊዝ መንግስት እና የቅኝ ገዥው ባለስልጣናቱ ስለህግ እና ስለሰው ልጅ ህይወት ክቡርነት የነበራቸውን የባህል እና የህሊና እድገት እንደሆነ እናውቃለን። በእንግሊዙ ቫይስሮይ ምትክ ህንድን በዘመኑ ያስተዳድር የነበረው የጀርመኑ ሂትለር ወኪል ቢሆን ኖሮ ጋንዲ እጣው ማን ይሆን ነበር። የኛዎቹ ወራሪዎች፣ መለስ ዜናዊ እና ግትልትሎቹ በጋንዲ ዘመን የነበረውን የእንግሊዝ የቅን ግዛት ቫይስሮይ እና የጦር አበጋዞቹን የሚመጥን የህግ እና የሞራል ሰብእና የተላበሱ ናቸውን? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሳይሰጥ ስለወደፊቱ ትግል ማውራት ታላቅ ስህተት ይሆናል።

## <u>፩- ቅንጅት፣ የሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል በቀጣይነት፣</u>

በኢትዮጵያ የሚደረገው የፖለቲካ ትግል ሰላማዊ እና ህጋዊ መሆን አለበት የሚለው የቅንጅት እና የመሪዎቹ እምነት ሀገራዊ እና ሕዝባዊ ጠቀሜታ ባላቸው ጠንካራ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘሩ አያስፈልግም። በድፍኑ ግን አንድ ህብረተሰብ የሰው እና የንብረት እልቂት

ሳይደርስበት፣ ሰላም እና መረጋጋት ሳይደፈርስ፣ መፈናቀል እና ስደት ሳይበራከት የቂም እና የበቀል አዙሪት አብቅቶ ከራሱ ጋር በመታረቅ በጋራ እና በህብረት መብቱን እና ጥቅሙን እያረጋገጠ የሚሄድበትን እድል የሚያመቻች የፖለቲካ ሂደት ጠቀሜታ እንዳለው ማንም አይክድም። የፖለቲካ ስልጣን በመያዝ ስም በሃገራችን የተቀሰቀሱ አመጻዎች ያደረሱትን ውድመት ለተረዳ፣ በጎራዴ የኖረ በጎራዴ ብቻ የሚጠፋበትን ሁኔታ በውስጡ ይዞ መውጫ ከሌለው የአመጽ አዙሪት ውስጥ እየደፈቀን፣ ከብልጽግና ከመብት መከበር እየራቅን፣ እንደ ሕዝብ እና እንደ ሐገር መኖር ከማንችልበት የገደል አፋፍ ላይ እንዳደረሰን በመረዳታቸው ነው የቅንጅት መሪዎች ለሰላማዊ እና ለህጋዊ ትግል በጽናት የቆሙት። ይህ እምነት ዞር ብሎ የራሱን ታሪክ ለመመልከት እዳይችል ልቡን እና ህሊናውን እንደ ደፈነው የመለስ ዜናዊ አመለካት ከፍርሃት የመነጨ አይደለም። ለነገሩማ የመለስ ዜናዊ የቆየ እና የትናንቱ ታሪኩ ከሚያሳየው በላይ በቅንጅት ውስጥ አርበኛነት እና ጀግንነት በደም ስሮቹ የሚፈስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ አለ። ቁም ነገሩ «ማን ከማን በላይ አነጣጣሪ፣ ማን ከማን በላይ ተኳሽ» መሆኑ ላይ ሳይሆን «ማን ከማን በላይ ሀገራዊ፣ ማን ከማን በላይ ሕዝባዊ እራእይ አለው» በሚል አዲስ እና ስልጡን መመዘኛ እንመዘን በማለት ቅንጅት ያሰበበት መንገድ በመሆኑ ነው፣ የሰላምን እና የህጋዊነት መንገድ የመረጠው።

እንደ እውነቱማ ከሆነ የቱ ነው ጀግናው? ትናንት ከጦር ሜዳ ሸሽቶ በጓደኞቹ ቸርነት ከሞት ቅጣት የተረፈው? ዛሬ ደግሞ እስከ ጥርሱ በታጠቀው አጋአዚ ጦሩ በእናቶች እና በህጻናት ላይ መትረየስ የሚተኩሰው «ጀግናው» መለስ ዜናዊ? ወይስ ይህን አይነቱን አረመኔ ሃይል ከብሩህ አይምሮ እና ከብእር ሌላ መከላከያ ሳይዙ በድፍረት ቆመው የሚታገሉት የራሳቸውን እና የወገኖቻቸውን ነጻነት እና መብት ለማስከበር ግብግብ የገጠሙት የቅንጅት መሪዎች። የቅንጅት መሪዎች እና መለስ ዜናዊ እና ግትልትሎቹ ስልጣን በተቆጣጠሩበት ሀገር፣ ነጻነት ያለመስዋእትነት እንደማይገኝ ያውቃሉ። ሰላማዊ ትግል ከሆነ ይህንን መስዋእትነት የሚከፍሉት በቅድሚያ መሪዎቹ እንደሚሆኑ ግልጽ ነው። ይህንን እውነታም ለሕዝብ አስረድተውታል። ሕዝብም የተከተላቸው በእዚህ ድፍረታቸው ነው።

እንደ ወያኔ መሪዎች በነጻ አውጭነት ስም ከገበሬ ጀርባ ተደብቆ የፈረደበትን ደሃ ገበሬ ፊት ፊት አስቀድሞ ገበሬ እየማገዱ መሪዎቹ ተደብቀው የሚያደርጉት ትግል እንዳልሆነ ስላወቁ ነው፣ የቅንጅት መሪዎች ሰላማዊ ትግልን የመረጡት። 17 አመት የጠመንጃ ትግል አደረግሁ የሚል የወያኔ ድርጅት፣ ከድርጅቶቹ መስራቾች መሃል ከሞላ ጎደል አንዱም ያልቆሰለበት አንዱም ያልሞተበት ሁኔታ መኖሩ በጦር አውድማ ማን ይማገድ እንደነበር የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ነው። የወያኔ መሪዎች በገበሬ ደም እና አጥንት እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን እንጂ በየጦር ግምባሩ ሲፈጁትን እና ሲያስፈጁት የነበረውን ደሃ ገበሬ ነጻ የማውጣት ህልም እንዳልነበራቸው በንቅዘት ከተሞላው የተንደላቀቀ ጉልታዊ ህይወታቸው ማስረጃውን እያገኘነው ነው።

ለቅንጅት መሪዎች ከሕዝብ ጀርባ ተሸሽጎ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ትግል በሞራል ኪሳራ የተሞላ፣ ግብዝነት እና ፍርሃት የተሞላበት ነው። ሰላማዊ ትግል የተመረጠው በሃገራችን በመፈጠር ላይ የነበረውን ሁኔታ ሁሉንም የሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ ወያኔኖችን ጨምሮ የሚጠቅም ነው ተብሎ ስለታመነበት ነው። የነጻነትን ትርጉም ጀግንነትን እና ሞራላዊ ስብእናን በአንድ ላይ ተዋህደው የሚከሰቱበት የትግል ሂደት የሰላም እንቅስቃሴው ነው፣ የሚል የጸና እምነት በቅንጅት አመራሮች በመያዙ ነው።

ይሁን እና ቀደም ብለን እንዳየነው የወያኔ መንግስት እና የባለስልጣኑ ማንነት ለእንዲህ አይነቱ ሰላማዊ እና ህጋዊ የሆነ የፖለቲካ ትግል ምንም ቀዳዳ ለመስጠት የሚያስችል አለመሆኑ፣ በሃገራችን ቅንጅት ለማካሄድ ያሰበውን የሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል በሚገባ መገምም እንዳለበት የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች በእጃችን ገብተዋል። የሰላማዊ እና ህጋዊ የትግል አመለካከት እና እምነት አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ይህን አመለካከት እና እምነት በስራ ላይ ማዋል የሚቻልበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ ሌላ ጉዳይ ነው። ባለንበት ሁኔታ ሰላማዊ ትግል የማድረግ ትክክለኛነት የሚካድ ባይሆንም፣ ይህ ሰላማዊ ትግል የወያኔን ፋሽስታዊ ባህርያት ግምት ውስጥ በማስገባት በአሰራር እና በአደረጃጀት ምን መምሰል እንዳለበት በቂ ጥናት እና ምርምር መደረግ አለበት።

***<u>ትግሉን በሰላማዊ እና በህጋዊ መንገድ መምራት ማለት ወያኔ ህገ መንግስቱን በመጣስ በቅንጅት እና በአባለቱ ላይ የሚያደርገውን ጥቃት መከላከል የሚችሉ ሰላማዊ የድርጅት አወቃቀር እና አሰራር በተግባር አለማዋል ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።</u>*** ሕዝብን ለተለያዩ የሰላም እንቅስቀሴዎች እራሱን እንዲያደራጅ እና እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ የሚደረገው ዝግጅት፣ እራሱን ከወያኔ አፋኞች እና ነፍሰ ገዳዮች የጥቃት ኢላማ እንዴት መከላከል እንደሚችል ግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን ይኖርበታል። ሰላማዊ ትግሉ አሁንም ቢሆን በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ድርጅታዊ ብቃት እና ዝግጁነት ላይ ከተመሰረተ በጣም አነስተኛ በሆነ የህይወት፣ የንብረት፣ የጊዜና የጉልበት ኪሳራ የፖለቲካ ለውጥ ማምጫ ሊሆን እንዲሚችል ሁላችንም ልንገነዘበው ይገባል። ምን አይነት እንቅስቃሴ? ምን አይነት አደረጃጀት? የሚሉት ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ማግኘት አለባቸው። ይህንን የማድረግ ሃላፊነት የቅንጅት አመራር ነው።

በሃገራችን ሕዝብ ህጋዊነትን ሲማጸን ህግ ማስከበር የሚገባው መንግስት ህገ-ወጥነትን ሲያስፋፋ፣ ሕዝብ የሰው ነፍስ በከንቱ እንዳይጠፋ ጥረት ሲያደርግ፣ መንግስት ዋናው ነፍስ አጥፊ፣ ሕዝብ ንብረትን ሲንከባከብ መንግስት ንብረትን ዘራፊ፣ የሆነበት የመንግስት ትርጉም መሰረታዊ ሚናውና ምንነቱን በጭንቅላቱ ያቆመ ሁኔታ በኢትዮጵያ ነግሷል። በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የመንግስት፣ የህግ ከለላ ተማምኖ በአደባባይ መንግስት ተቃውሞ መደራጀት ይቻላል ወይ? የሚለው ጥያቄ መልስ ይሻል። አንድ ትግል ህጋዊ የሚሆነው ሰላማዊ ስለሆነ? ወይስ በአደባባይ ስለተደራጀ? በአደባባይ የመደራጀት መብት የመንግስት ገዳዮች ኢላማ የሚያደርግ ከሆነ፣ ህገ መንግስታዊ የሰላም ተቀውሞ የማድረግ መብታችንን በድብቅ ማድረግ ምን ስህተት ይኖረዋል። እራሳችንን ከአመጽ እስከ አራቅን ድረስ የምናደርገው ትግል ህጋዊ ብቻ ሳይሆን ሞራላዊ ጭምር ነው። በድብቅ እየተደራጁ እራስን ሁኔታው ለሚፈቅዳቸው ጠንካራ የሰላማዊ ትግሎች ማዘጋጀት የሀገራችን ልዩ ሁኔታ የጫነብን እዳ ነው። ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ጠንካራ ድርጅታዊ አቅም ማዳበር ይጠበቅብናል። ከእዚህ በተረፈ ግን ቅንጀት የሰላማዊ ትግል በወሰነበት ወቅት ባወጣው መግለጫ ላይ የቀረቡትን የመታገያ ነጥቦች እና ሌሎችንም አዳዳዲስ የመታገያ ነጥቦች፣ እንደ ሁኔታው እየገመገሙ በመጨመር የሰላማዊ ተቃውሞ ትግል ማፋፋም ይኖርብናል። ባለፉት ጥቂት ገጾች የተነሳው የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ እና የቅንጅት መሪዎች መፈታት ጥያቄ እርስ በእርሳቸው የተጎናጎኑ ናቸው። የታሰሩት የቅንጅት፣ የሙያ እና የሲበቪክ ማህበራት፣ ነጻ ጋዜጠኞች፣ የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ የሚገለጽባቸው ተምሳሌቶች ናቸው። በፖለቲካ ምክንያት ያለአግባብ የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ፣ የነጻ ተቋማት ምስረታ እውን ይሁን፣የሚለው መፈክር የወቅቱ የመታገያ መፈክራችን መሆን አለበት።

ሕዝብን ለከፍተኛ የወያኔ ጭፍጨፋ በማያጋልጡ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ የትግል አቅጣጫዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው:: የወያኔን የኢኮኖሚ አውታሮች ማዳከም፣ በወያኔ ድርጅቶች የሚመረቱ ማንኛቸውም አይነት ምርቶች አለመግዛት፣ የወያኔን ራዲዮ እና ቴሌቪዥን አለማየት በነጻ ጋዜጣነት ስም የወያኔ ሰላዮች የሚያሳትሟቸውን ጋዜጦች አለመግዛት፣ ከወያኔ ጋር ቅርበት ያላቸውን የወያኔን ጨፍጫፊ መንግስት ለማጠናከር ከወያኔ ጋር በሽርክና የሚሰሩ የንግድ ተቋማትን ምርት እና ሌሎችንም ግልጋሎቶች አለመግዛት፣ የወያኔ ሰላዮች መሆን በጥቆማ በግድያ በሕዝብ ሃብት ዘረፋ የተሰማሩትን ግለሰቦች፣ ማግለል እነዚህ ሁሉ ህጋዊ እና ሰላማዊ የትግል መስመሮች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው::

በተለያዩ አጋጣሚዎች ስብሰባዎች እና ሌሎችም ሕዝብ በስፋት ቢሚገኝባቸው በአሎች ላይ፣ በሙሉ ሕዝብ ለወያኔ ያለውን ተቃውሞ እና ንቀት ሰላማዊ በሆነ መንገድ መግለጽ፣ ለወያኔ ባለስልጣናት ወይም ከእነዚህ ባለስልጣናት ጋር ለሚሞዳሞዱ ሆዳሞች ምንም አይነት ክብር አለመስጠት፣ በየፋብሪካው፣ በየመስራቤቱ፣ በየትምህርት ቤቱ አቅም በፈቀደ መጠን ወያኔ በሕዝብ ላይ የጫነወን አምባገነናዊ እርምጃዎች ሁኔታው በሚፈቅደው መንገድ መቃወም:: በስራ መለገም፣ ትምህርት ማቆም ወዘተ እርምጃዎችን መውሰድ፣ በቁጥር አንድ ግለሰብ እንኳን ቢሆን፣ ህጋዊ በሆነ መንገድ ሊከበርለት የሚገባው ህገመንግስታዊ መብቱ አንድ በመሆኑ ብቻ የሚገደብ ባለመሆኑ በጥቂት ደፋሮች አማካይነት በሚደረግ እንቅስቃሴ ህጋዊ የሆኑትን መብቶች በሙሉ በስራ ላይ ለማዋል በመንቀሳቀስ ለፍትህ ስርአቱ ፈተና መስጠት:: ለምሳሌ ሕዝብን የካዱ የፓርላማ ተመራጮች በህገመንግስቱ ውስጥ በተጻፈው ህጋዊ አንቀጽ መሰረት በሕዝብ ፊርማ አማካይነት ከፓርላማ እንዲነሱ በመጠየቅ መንግስትን እና የፍትህ ስርአቱን ማጋለጥ:: የሰላማዊ ሰልፍ እና ሌሎችንም ፈቃዶች በማግኘት የሕዝብ ተቃውሞ ማደራጀት፣ የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊ አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ በየግዜው የሚደረጉ የአንድ ቀን የቤት ውስጥ የመቀመጥ አድማዎችን ማድረግ፣ በተባለው የአድማ ቀን ከቤት ባለመውጣት ለወያኔ ገዳዮች ኢላማ አለመሆን::

እነዚህ እና እነዚህን የመሳሰሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባናል:: ከሁሉም በላይ ትግሉ የአንድም ሰው ህይወት እንዳይባክን ንብረት እንዳይጠፋ ከመንግስት ገዳዮች ጋር ፍጥጫን ያስወገደ መሆን ይኖርበታል:: ሕዝብ በጽሁፍ እና በኤሌክትሮኒክ ስልቶች መረጃ ማግኘት የሚችልባቸውን መንገዶች ማጠናከር:: እንደ ትንሳኤ የመሳሰሉትን እና ሌሎችን ሬድዮ ጣቢያዎች ሕዝብ እንዲያውቃቸው እና እንዲሰማቸው ማድረግ፣ እነዚህን የመሳሰሉ ሬድዮ ጣቢያዎች እንዲጠናከሩ በገንዘብም በሰው ሃይልም መርዳት፣ ከላይ በተዘረዘሩት እና ሌሎችንም በከፍተኛ ጥንቃቄ በሚጠኑ ዝርዝር የትግል ስልቶች፣ የወያኔን ዘረኛ እና አምባገነን ስርአት መታገል ይኖርብናል:: <u>እንዲህ አይነቱን የትግል ስልት በአግባቡ በስራ ላይ ለማዋል የሚችል የአመራር አካል በሃገር ውስጥ ማጠናከር ይኖርብናል:: ከእዚህም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ላለው አመራር ከፍተኛ ድጋፍ መስጠት የሚችል ራሱን የቻለ የፖለቲካ ቡድን ከሃገር ውጭ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል:: ይህ ጉዳይም የራሱ ዝርዝር ጥናት ያስፈልገዋል::</u>

ቅንጅት እና የውጭ ሃገሩ እንቅስቃሴ አሁን በተፈጠረው አጠቃላይ ቀውስ በውጭ ሃገር የሚደረገው እንቅስቃሴ በተጠናከረ መልኩ መቀጠል አለበት:: ሆኖም ግን ወቅቱ የሚያስፈልገውን የአደረጃጀት ጥራት

እና ብቃት ይዞ መንቀሳቀስ አለበት:: የውጭው የመታገያ ነጥብ ያው እንደሃገር ቤቱ በነጻ ተቋማት ምስረታ እና በቅንጅት መሪዎች፣ አባለት፣ ደጋፊዎች ጋዜጠኞች እና ሌሎችም የህብረተሰቡ አካለት መፈታት ላይ ያተኮረ ይሆናል::

የቅንጅት አመራር እስር ቤት ባልገባበት ወቅት የውጭውን ኢትዮጵያዊ ለማደራጀት አስቦ የነበረበትን የማደራጃ ሃሳብ የተቀበለ ነገር ግን አሁን ከተፈጠረው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ማስተካከያ ማበጀት ተገቢ ነው:: የውጭው እንቅስቃሴ አሁን የሚሰራቸውን ሶስት መሰረታዊ ስራዎች፣ የገንዘብ ማሰባሰብ፣ የሕዝብ ማንቀሳቀስ ፣ የአባላት መመልመል ስራ እና የሎቢ ስራ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ከእዚህ በተረፈ ከእነዚህ ጉዳዮች ውጭ የቅንጅት የድጋፍ ኮሚቴዎች በተለምዶ ከሚሰሯቸው ስራዎች በተለይ የሃገር ቤቱ ትግል እየጠየቃቸው ያሉትን ከአመራሩ ጋር በመተባበር ለሚሰሩ የፓርቲ ስራዎች እራሱን የቻለ የፓርቲ መዋቅር እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነው:: <u>**ያለንበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ዴሞክራሲያዊነትን እና ጥንቃቄን በአንድ ላይ በማዋሃድ በጊዚያዊነትም ቢሆን መቋቋም የሚገባው ከፍተኛ የፓርቲን ሃላፊነትን የሚጠይቅ ስራ የሚሰራ አካል ያስፈልጋል::**</u>

እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት የድጋፍ ድርጅቶችን ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀት የበለጠ የሚያጠናክር ሁሉን አቀፍ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርበታል:: የፓርቲው ጊዚያዊ መዋቅር ስራዎች፣ ከድጋፍ ድርጅቱ ስራዎች ጋር ተደራራቢ እንዳይሆን፣ በድጋፍ ድርጅቱ ዴሞክራሲያዊ ባህርይ ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር አድርጎ መቀጠል ይኖርበታል:: ፈጠራን እና ተነሳሽነት የማይገድል መሆን ይኖርበታል::

በፓርቲው ጊዚያዊ መዋቅር ውስጥ ከነባሮቹ የፖለቲካ ድርጅች የተውጣጡ ግለሰቦች እንዲኖሩ በማድረግ ከእዚህ ውጭ ግን በችሎታቸው፣ በእምነት ጽናታቸው እና በስነምግባራቸው የተመረጡ፣ እስካሁን በደጋፊነት ሲሰሩ የነበሩ ብቃት ያላቸውን ሰዎች ማሳተፍ ተገቢ ይሆናል:: ከእዚህ ውጭም በማንነታቸው ላይ ጥርጣሬ የሌለንን ብቃት እና ጽናት ያላቸውን ግለሰቦችም ለማስተናገድ መሞከሩ አይጎዳም:: በእዚህ መስፈርት አማካይነት ለእንዲህ አይነቱ ድርጅት የሚሆኑትን ሰዎች በመምረጥ **የየሀገሩ እና የየስቴቱ ጠቅላላ ጉባኤዎች የሚጫወቱት ሚና እንዳለም ማጥናት ተገቢ ይሆናል::** ለማንኛውም በቅድሚያ ለተለያዩ ስራዎች እና ኮሚቴዎች የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል አንጥሮ ካስቀመጠ በኋላ፣ ለጊዚያዊ የፓርቲው ኮሚቴ የሚሆነው የአባላት ቁጥር በመወሰን መንቀሳቀስ ያስፈልጋል:: ለሴቶች፣ ለወጣቶች ለተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች፣ ለተለያዩ ብሄረሰብ አባለት ትኩረት የሰጠ አመላመል ያስፈልጋል:: ከእዚህ በላይ የቀረበው ሃሳብ በፍጥነት እና በዝርዝር ተጠንቶ በስራ ላይ መዋል ይገባዋል::

## <u>*7-ቅንጅት ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ እና ፖለቲካዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ የመስራትን አስፈላጊነት በሚመለከት:-*</u>

ቅንጆት ሁሌም ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚያደርገው ህብረት በቅድሚያ የሚመለከተው ህብረቱ ሃገርን እና ሕዝብን የሚጠቅም ነወይ? ከሚል ግምገማ በመነሳት ነው:: በሃገር ውስጥ በተለያዩ የቅንጆቱ አባል ድርጅቶች የተፈጠረው አንድነት፣ ቅንጆቱ የፖለቲካ ስልጣን ቢይዝ በተግባር የሚያውላቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎች በጋራ በመስማማት ነው:: ለፖለቲካ ስልጣን የሚደረግ ህብረት የተለየ ጥልቀት እና ጥራት ያለው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ስምምነትን የሚጠይቅ ነው::

ከእዚህ ውጭ ወቅታዊ የሆኑ የጋራ ችግሮች ለመቅረፍ የሚደረግ መተባበር አለ:: ቅንጅት በህብረቱ ውስጥ ከነበሩ ሁለት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር (ከአብኮ እና ከደቡብ ህዝቦች ጋር ማለት ነው) በምርጫው ወቅት ያደረገው መተባበር በእዚህ እምነት ላይ የተመሰረተ ነበር:: በምርጫው ወቅት ወያኔ የሚያደርሰውን ተጽእኖ በጋራ ለመታገል፣ በጋራ ለሕዝብ እና ለአለምአቀፉ ማህረሰብ ለማስረዳት በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ተቃዋሚውን የሚጎዳ፣ ድምጹን የሚከፋፍል፣ መጠላለፍ እንዳይፈጠር ለማድርግ በጋራ ጥረት ብዙ ተሰርቷል:: እንዲህ አይነቱ ትብብር ምርጫውን ማእከል ያደረገ እና ከምርጫው ጋር የሚነሱትን በወያኔ የሚፈጠሩ ችግሮች በጋራ ለመታገል አስቦ የተተገበረ ነበር::

ዛሬ ያለንበት ችግር ከምርጫው በፊት ፣ በምርጫው ወቅት እና ከእዘም በኋላ ከነበረው ሁኔታ የተለየ ነው:: የሕዝብ ድምጽ እንዲከበር በጋራ ቅንጅት እና በህብረቱ መሃል ይደረግ የነበረው መተባበር የሀገር ቤቱ የህብረት ድርጅቶች ፓርላማ ከገቡ በኋላ አበቅቶለታል:: በእዚህ ድርጊታቸው ትግሉን ክፉኛ ጎድተውታል:: ህብረቱ እና ቅንጅቱ በጋራ ጀምረውት የነበረውን የሕዝብ መብት ይከበር የሚል ጥያቄ በጋራ ገፍተውበት ቢሆን ኖሮ ዛሬ በሃገራችን የተለየ ሁኔታ ይኖር ነበር:: ይህ ሲባል ግን ቅንጅትም እንደ ድርጅት ፓርላማ በመግባት እና ባለመግባት የጠራ አቋም ይዞ አለመንቀሳቀሱ፣ እንዲያውም አስከመጨረሻው ቀን ውሳኔ ላይ አለመድረሱ ለህብረቱ ድርጅቶች ፓርላማ መግባት፣ የራሱ አስተዋጽኦ አላደረገም ማለት እራሳችንን ማታለል ይሆናል:: አንዱ አንዱን እየጠበቀ፣ አንዱ አንዱን እየፈራ በኖረበት ሃገር፣ በፓርላማ መግባት እና አለመግባት ጥያቂ ላይ አስቀድሞ የጠራ አቋም በጋራ ለመያዝ አለመቻሉ የተከሰተውን መከፋፈል እና የተፈራውን ለወያኔ ጥቃት መጋለጥ አስከትሏል:: የተጠራው ሕዝባዊ እና ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ የሕዝብ ድምጽ ተጭበርብሯል የሚል እምነት በነበራቸው ድርጅቶች በሙሉ ተደግፎ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ካሁኑ የተለየ ይሆን ነበር::

አሁን ያለንበት ሁኔታ ከምርጫው በፊት እና በኋላም በወያኔ ሲፈጸሙ የነበሩት ችግሮች በተባባሰ መልኩ መቀጠላቸውን የሚያሳይ ነው:: የተቀየረ ነገር ቢኖር በሕዝብ ላይ የሚደርሰው የግድያ እና የሰብአዊ መብት እረገጣ መባባሱ ይህ ጥቃት ደግሞ ከማናቸውም ድርጅቶች የበለጠ ፓርላማ አልገባም ባለው የቅንጅት መሪዎች እና ደጋፊዎች ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው:: ከእዚህ ውጭም ከምርጫው በፊት የነበረችው ትንሽም ብትሆን የህግ እና ነጻነት አስከባሪነት፣ ወያኔያዊ አስመሳይነት ጭልጥ ብላ የጠፋችበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: የሕዝብ ድምጽ ይከበር የሚሉ፣ በምርጫ ቦርድ እና በፍርድ ቤት በመሄድ የሚደረጉ ሙከራዎች የትም ያልደረሱበት ሁኔታ ተረጋግጦ፣ እነዚህን እና ሌሎችንም መንግስታዊ ተቋማት ከገዠው ፓርቲ ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ የመዋቀራቸውን አስፈላጊነት የተረዳ ትግል ተጀምሯል:: ቅንጅት በወያኔ የተጭበረበረው 299 የፓርላማ ምርጫ ጣቢያ ድምጽ ይጣራ እና የሕዝብ ድምጽ ይከበር የሚለውን ጥያቄ ከስምንቱ የቅድመ ሁኔታዎች መሃል ያላስገባው ከነጻ ተቋማት ምስረታ በፊት ይህንን ጥያቄ ምንም አይነት መልስ ማግኘት እንደማይችል ስለተረዳ ነው:: ጥያቄው የ299 ድምጽ የማስከበር ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱን የቅርብ እና የሩቅ ዴሚክራሲያዊ የፖለቲካ ህይወት የሚወስኑት የነጻ ተቀዋማት ምስረታ ነው የሚል እምነት ላይ ስለተደረሰ ነው::

በሂደት የተቀየረው የሃገሪቱ ሁኔታ ማን ከማን ጋር፣ በምን ጉዳይ እና እንዴትስ በህብረት መታገል ይችላል የሚሉትን ጥያቄዎች አስነስቷል። ያም ተባለ ይህ፣ አሁን ያለው አሳሳቢ ሁኔታ የተቻለውን ያህል ስፋት ያለው ህብረት መፈጠር እንዳለበት የሚጠቁም ሆኗል። ህብረት ከማን ጋር፣ ለምንስ አላማ፣ እንዴትስ፣ የሚሉ ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው። ለምሳሌ ያክል ከምርጫው በፊት በውጭ ሃገር የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት የሀገር ውስጡን ትግል አይጠቅምም የሚል ምክንያት ቅንጅት ነበረው። አሁንስ በውጭ ሃገር የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በሃገር ውስጥ ለሚደረገው ትግል ምን አስተዋጽኦ ያድርጋሉን? ሃገር ቤት ምንም አይነት አካላዊ ድርጅት ሳይኖራቸው ትግሉን እንዴት ሊደግፉ ይችላሉ? ከውጭ ተቀምጦ ጥሪ በማድረግ ብቻ የሕዝብን ትግል መምራት ይቻላል ወይ? በሌላ በኩልም ወያኔ በወሰደው እመቃ የተነሳ ከመቼውም የበለጠ ከፍተኛ የዲፕሎማሲያዊ ትግል ማድረግ የሚያስፈልግበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ይህ ሁኔታ በውጭ የሚገኘው የቅንጅት ደጋፊ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶችን የተባበረ ትግል አስፈላጊ አድርጎታል። በወያኔ ላይ በውጭ መንግስታት በኩል የሚያደርጉት ተጽእኖ ለትግላችን ቀላል ያልሆነ ትርጉም አለው። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል አንድ አካል ሆኗል። እዚህ ላይ መደረግ የሚችል ህብረት አለ ወይ? ይህ ህብረት በምን ግልጽ አጀንዳዎች ዙሪያ ይሆናል? በሲቪክ ማህበረሰብ ስም የሚቀርብ የህብረት ጥያቄ አለ። በውጭ የሚገኙ የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት ጋርም፣ በጋራ መስራት ስለሚቻልባቸው ጉዳዮች በዝርዝር ማወቅ ይጠይቃል። በውጭ ሃገር የሚደረገውን ትግል በጋራ እንምራው እናስተባብረው የሚለው ጥያቄ በጋራ አላማ ላይ ግልጽነት እስካለው ድረስ ምንም ችግር አይኖረውም። ግን በሌላ በኩል አንዳንድ ሲቪክ ማህበራት እና በውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች የሃገር ቤቱን ትግል የሚመራው አካል ጠፍቷል ወይም ተዳክሟል በሚል ምክንያት ትግሉን በጋራ እንምራው የሚል ጥሪያቸው ትርጉሙ ምንድነው? በጋራ እንስራ ቢባልስ በሃገር ቤት የሚደረገውን ጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ እንዴት መምራት ይቻላል። ቅንጅት በሃገር ቤት ውስጥ አመራር አለው። በእዚህ አመራር ግምገማ ላይ የተመሰረተ የቅንጅትን ድርጅታዊ ጥንካሬ እና ዝግጁነት በመመርመር የተለያዩ እንቅስቃሴ-ች ሊያቅድ ይችላል። ሌሎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሳሳይ የሆነ ግምገማ ማድረግ ይችላሉ ወይ? በሀገር ውስጥ ካለው የቅንጅት አመራር ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩ መዋቅሮችና ግለሰቦች አላቸው ወይ? ወይስ ቅንጅት የሚጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ፣ የስራ ማቆም አድማ እና ወዘተ ዝም በሎ ከውጭ ከመደገፍ ሌላ ምን ማድረግ ይቻላሉ? እንዲህ ከሆነ የጋራ ህብረቱ ከስም ያለፈ ትርጉም ይኖረዋል ወይ?

በሃገር ውስጥም ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚፈጠር ህብረት ለምን አላማ? ከማን? እንዴት በህብረት መስራት ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎች ያስነሳል። እዚህም ላይ ቢሆን አጅግ ስፋት ያለውን ጸረ-ወያኔ ህብረት መፍጠር ያስፈልጋል። በአንድ በኩል ወያኔ ህጋዊ እውቅና የለውም የሚለው በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ የሚደገፈው እስር ቤት እና ከእስር ቤቶች ውጭ ባሉት አመራሮች የሚመራው የቅንጅት እንቅስቃሴ እንዴት አድርጎ ነው በፓርላማ ውስጥ በህጋዊነት ከሚንቀሳቀሱት ኦብኮን እና ሌሎችንም አብኮን ከመሰሉ ድርጅቶች ጋር ህብረት መፍጠር የሚችለው? አጀንዳዎቹስ ምን ይሆናሉ? በቅንጅት ስም ተመርጠው በግላቸው ፓርላማ የገቡትስ ግለሰቦች እና የቅንጅት ግንኙነት ምን ይሆናል? የቅንጅት አመራር አሁን ባለበት ሁኔታ የጸረ-ወያኔ ሰላማዊ ትግሉን ለብቻው በሚገባ ተደራጅቶ ከመምራት ውጭ ሌላ ምን አማራጭ አለው። ሕዝቡ እና ያለንበት ሁኔታ ከቅንጅት ውጭ ለሚሞከር አመራር ቦታ ይሰጣል ወይ?

ይህም ተብሎም በሀገር ውስጥም ሆነ በሃገር ውጭ የሚገኙትን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራትን በአንድ ላይ በማስተሳሰር የሚሰሩ ስራዎች እንዳሉ መካድ አይገባም።

በሀገሪቱ ሕዝቦች ላይ በአጠቃላይ፣ በተለይ በፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፣ አባለት እና ደጋፊዎች ላይ በጋዜጠኞች፣ በሲቪክ ማህበራት መሪዎች ላይ እደረሰ ያለውን የግድያ የእስራት እና የእንግልት ግፍ ለማጋለጥ፣ ለማስቆም በሃገር እና በሃገር ውጭ የሚደረጉ ትግሎችን በጋራ ማቀናጀት ይቻላል። በእዚህ ጉዳይ ላይ የታሰሩ እንዲፈቱ፣ ግፈኞች ለፍረድ እንዲቀርቡ፣ በሃገር ውስጥ ከሚደረገው የተባባረ ትግል በተጨማሪ፣ በውጭ ሃገራትም እንዲህ አይነቱ ሁኔታ እንዲወገድ የፖለቲካ ወታደራዊ እና ኢኮኖሚዊ ድጋፍ ለወያኔ በሚሰጡ መንግስታት ላይ በዲፖሎማሲያዊ መንግድ በሚደረግ ትግል ተጽእኖ ለማድረግ በጋራ መንቀሳቀስ ይቻላል። እንዲህ አይነቱ ህብረት በጋራ ጥሪት ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነውን፣ አቅሙ እና ችሎታው ያለውን ድርጅት፣ ቡድን እና ግለሰብ ሁሉ ያካተተ ሊሆን ይገባዋል። ቅንጅት እንዲህ አይነቱ ህብረት እንዲፈጠር ስራውን በተገቢውም መንገድ እንዲሰራ የሚያስችለውን አቅድ በቅድሚያ በማዘጋጀት የድርጅቱን ትልቅነት የሚያንጸባርቅ ቀና እና ተምሳለታዊ መሆን የሚችል አመራር መስጠት መቻል አለበት። በዋንኛነት እንደዚህ አይነት ፍላጎት ያላቸውን ሃይሎች በጋራ የሚገኛኙበትን መድረክ በመፍጠር የሰው ጉልበት፣ ገንዘብ እና እውቀት ሳይባክን በጋራ ስምምነት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ ስራ እንዲሰራ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ አይነቱ ህብረት በየደረጃው በሚደረግ መቀራረብ እና መግባባት በጋራ በሚከናወኑ ስራዎች እና በሚገኙ ድሎች እየተጠናከረ ጥልቀት እያገኘ የሚሄድ መሆኑን አስቀድሞ ማወቁ ተገቢ ነው። የገጠመንን ፈተና በሚገባ ተረድተን ትረጉማቸው ሕዝብን እና ሃገርን በሚያስቀድሙ ጉዳዮች ላይ በማተኮር መከፋፈል እና መለያየት፣ እንዲሁም ለጠባብ የድርጅት እና የግል ጥቅሞች ስንል ለዝንተ አለም ስናደርገው የኖረውን ጎጂ ባህል እና ድርጊት በወንድማማችነት እና የእህትማማችነት ወገናዊ አንድነት ተክተን መጓዝ መቻል አለብን። ቅንጅት በምርጫ ወቅት የሕዝብን ምናብ የሰባበትን የፍቅር መፈክር ከፍ አድረጎ በማንሳት ዛሬም እጁን ለሰላም ለአንድነት መዘርጋት ይኖርበታል።

ከእዚህ በተጨማሪ ቅንጅት ያነሳቸው እና መሪዎቹም የታሰሩላቸውን የሃገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ከስሩ መንግለው የሚጥሉትን እና በሕዝብ የሚደገፉትን የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ የጋራ የመታገያ አጀንዳ አድርጎ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ በጋራ መታገል ይቻላል። ይህ የጋራ ትግል፣ በጋራ ከሚደረጉ በተለይ በውጭ የሰልፍ እና የዲፕሎማሲያዊ ትግል መደገፍ ይቻላል። በውጭ ሃገር የሚገኘው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በድርጅቶች እና በቡድኖች ፉክቻ ሃገራዊ እና ወገናዊ ስሜቱ መጎዳት የለበትም። ችግሮች ካሉም ሕዝብ ፊት በውይይት እንዲፈቱ በማድረግ ሃይላችንን ገንዘብ እና አውቀታችንን በወያኔ ላይ ማነጣጠር አንችላለን። ነገር ግን አሁን በውጭ እየተነሳ ያለው የጋራ አመራር የመስጠት ጥያቄ ወይም የመተባበር ጥያቄ፣ በሃገር ውስጥ ለመተግበር ሲታሰብ እንደ ውጭው ቀላል እና ቀጥተኛ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው በቅንጅት በኩል የሃገር ቤቱ ትግል ሃገር ውስጥ በሚገኘው አመራር በጥናት እና በግምገማ ላይ የተመሰረተ ድርጅታዊ ወጥነትን ይዞ የሚሰጥ አመራር ነው። እንዲህ አይነቱን አመራር ባሁኑ ወቅት እንዴት አድርጎ ከሌሎች በሀገር ቤት ውስጥ በአካል ከማይገኙ ድርጅቶች አመራር ጋር አቀናጅቶ ለመስራት እንደሚቻል ማሰብ አይቻልም። ግልጽ የሆነ የጋረ የመታገያ አጀንዳ

እስካለ ድረስ ግን በየወቅቱ የሚቀየሩ ሁኔታወች የሚያመጧቸውን አዳዲስ እውነታዎች በማየት በሃገር ውስጥም ቢሆን በአንድነት መታገል የማይቻልባቸው ምክንያቶች አይኖሩም:: ከሁሉ በላይ ግን በጸረ ወያኔ ትግል የተሰለፉ እና አሁን የተያዘውን የነጻ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ምስረታ የትግል ጥሪ የሚጋሩ ሃይሎች በሙሉ በራቸውን ከፍት በማድረግ፣ በተዘዋዋሪ፣ በአግቦ፣ በአሉባልታ እና በሽሙጥ ሳይሆን፣ በፊት ለፊት ለመነጋገር የሚችለበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው::

## ***፱- ቅንጅት እና የአመጽ ትግል የሚያኪያሂዱ እንቅስቃሴዎች፣***

ወያኔ ምርጫውን የተጠቀመበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት ለመገንቢያ ሳይሆን የዜጎችን የፖለቲካ ማንነት ለመሰለያ ነው:: ዛሬ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ዘረኛነትን፣ መከፋፈልን እና ሀገራዊ ውርደትን የሚቃወም፣ ለቅንጅት እና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ማናቸውንም ድጋፍ የሰጠ፣ ወይም የመስጠት አዝማሚያ ያሳየን ግለሰብ፣ በሞት፣ በእስራት እና በስደት እዲቀጣ እየተደረገ ነው:: ገበሬው በፖለቲካ እመቃው የተነሳ ከመሬቱ እየተነቀለ በሌሎች ገጠሮች እና ከተሞች እተሰደደ ነው:: ከተሜው ከመኖሪያ ከስራው እና ከንግዱ እየተነቀለ ወደሌሎች ከተሞች እና አጎራባች ሃገሮች እተሰደደ ነው:: ዛሬ በሃገረችን ዘረኞች እና ባንዳዎች የሚያኪሂዱት ሁለተኛ ዙር ቀይ ሽብር እየተካሄደ ነው:: ሌላ ዙር የተማረ የሰው ሃይል ግዞት፣ ሌላ ዙር የሃገር ወዳዶች ስደት ተጀምሯል:: ቅንጀት ጭንቅላቷን አሸዋ ውስጥ ቀብራ ተደብቂያለሁ በማለት እራሷን ማሞኘት እንደምትፈልገው ሰጎን መሆንን አይፈልግም:: በሃገራችንን ቀድሞውኑ የጠመንጃ ትግል ያደርጉ በነበሩት የተለያዩ ቡድኖች ላይ አዳዲስ በርካታ ቡድኖች እየተመሰረቱ እንደሆነ በቂ መረጃ አለው::

መንግስት የንብረት እና የህይወት መከላከያ መሆኑ ቀርቶ ዋናው የህይወት እና የንብረት ጠር በሆነበት ሃገር፣ እራሱን ከመንግስት ገዳዮች እና ዘራፊዎች የመከላከል ተፈጥሯዊ መበት እንዳለው የሚያምነው ሰው ተበራክቷል:: ዛሬ ወያኔ የሚያኪያሂደው ፋሽስታዊ እመቃ የሕዝቡን ሰላማዊ የፖለቲካ ፍላጎት እየገደለ ሃገራቱን እንደገና ወደ ሌላ የአመጽ አዙሪት ውስጥ እየደፈቃት ነው:: የሰላም እና የህጋዊ የፖለቲካ ህይወት እንዳይኖር ጉልበቱን እና መሳሪያውን በመተማማን በሕዝብ ላይ ግፍ እየፈጸመ ያለው የወያኔ ቡድን ሕዝብን ወደ አመጽ መንገድ እየገፋፋ የሚገኘ ብቸኛ ወንጀለኛ ነው:: በሰው ህይወት፣ በንብረት፣ በሰላም እና መረጋጋት መጥፋት ተጠያቂው ይህ አመባገነን መንግስት እና በውስጡ አገልጋዮቹ የሆኑት ሆድ አደር ባለስልጣኖቹ ናቸው:: አሁንም የወያኔን አገልጋዮች እናሳሰባቸዋለን:: ዛሬ በሕዝብ ላይ ግፍ የሚፈጽሙ ሁሉ ነገ በሕዝብ ተጠያቂ መሆናቸው የማይቀር ነው::

በሌላ በኩል ዛሬ በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በመጠቀም መሳሪያ ለማንሳት የሚሽቀዳደሙ ቡድኖች ሁሉ ትናንት በተመሳሳይ መንገድ መሳሪያ በሕዝብ ስም አንስተው ስልጣን ከያዙ፣ ሕዝብ በዳዮች የማይሆኑበት ምክንያት ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ ቅንጅት ያነሳል:: የዛሬው ነጻ አውጪ ልክ እንደወያኔ የነገው አምባገነናዊ ስርአት እርሾ እንደማይሆን ምን ዋስትና አለው? ብሎ ቅንጅት ይጠይቃል፣ እራሳቸውንም እንዲጠይቁ ይፈልጋል::

ጠመንጃ መንከስ ከሚቀናው ባህላችን እና በሕዝብ ላይ ከሚደርሰው ግፍ በመነሳት መሳሪያ ማንሳት ቀላል ነው:: ከባዱ ነገር በዳይን ማጥቃት እና ማሸነፍ አይደለም:: የፈለገውን ያህል ግዙፍ ሰራዊት ቢኖራቸውም

ሕዝብን እየበደሉ ለዘላለም መኖር እንደማይቻል ለማወቅ ያለፉት አስርተ አመታት የሃገራችን ታሪክ በቂ ትምህርት ሰጥቶናል። ችግሩ አመጽ አንዱን አምባገነን በሌላ አምባገነነን የሚተካ መሳሪያ መሆኑ ብቻ ነው። በሕዝብ ላይ እወረደ ካለው መአት እና ቅንጅት ዛሬ እራሱ ካለበት ሁኔታ በመነሳት በአመጽ መንገድ ለመሄድ ለሚፈልጉ እና እሄዱ ባሉ የአመጽ ቡድኖች ላይ ምንም ማለት የሚችልበት የአቅምም እና የሞራል የበላይነት የለውም። ይህ እንዳይሆን ያደረገው በሕዝብ ፊት ከፍተኛ ተደማጭነት ያላቸውን የሰላም እና የህጋዊነት ሃዋርያት የሆኑትን የቅንጅት መሪዎች በጉልበት እና በህገ-ወጥነት ለእስር የዳረገው ወያኔ ነው። ቅንጅት እንደ ድርጅት ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመታገል በመነሳቱ፣ መንግስት ሰላምን በማደፍረስና ህግን በመጣስ የሰነዘረበትን ጥቃት ዘንግቶት አይደለም፣ አሁንም ሰላም የሚለው። ዞሮ ዞሮ የሃገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ሰላማዊ በሆኑ፣ የውይይት እና የመግባባት ስልቶች ለመፍታት ከመሞከር ውጭ ሌላ የተሻለ አማራጭ አለ ብሎ ስለማያምን ነው። መንግስት ህገወጥነት እና ሰላምን የሚያስፋፋው ዋንኛው ወኪል በሆነበት ሃገር፣ የቅንጅትን የሰላማዊ እና ህጋዊ የትግል ስልት የሚጠራጠሩ በርካቶች ቢሆኑም፣ ቅንጅት ግን አሁንም ወደፊትም ለሃገር እና ለወገን የሚበጀው በተጠናከረ እና በተደራጀ መንገድ በእዚሁ መቀጠሉን ነው።

***አንዳርጋቸው ጽጌ***

***December 2005***

አስተያየት ለመስጠት በ atsege@hotmail.com ተጠቀሙ፤